# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በግብርና ሚኒስቴር
## የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ
## የተከናወነ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2003 ዓ.ም

# ማውጫ


**ክፍል አንድ ....................................................................................................................1**

*ማጠቃለያ* /Summary/ ------------------------------------------------------------------------------- 1

*መግቢያ*---------------------------------------------------------------------------------------------------5

*የግብርና ሚኒስቴር ራዕይና ተልዕኮ* .....................................................................................6
*የግብርና ሚኒስቴር ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር* ......................................................................6
*የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት* .................................................................................................7
*የሰው ሃይል*...........................................................................................................................7
*የፋይናንስ ምንጭ* .....................................................................................................................7
*የኦዲቱ አላማ* ..........................................................................................................................7
*የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና ጭብጦች* .............................................................................8
*የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች* /Evaluative Criteria/ .............................................................8
*የኦዲቱ ወሰን ና ዘዴ/ሥልት/* .....................................................................................................9

*የአሰራር ሂደት መግለጫ* (Process Description)------------------------------------------------ 10

*የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ያለው የሥራ ሂደት፡-* ...........10
*የ ንስሳትና ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት*.......................................................................11

**ክፍል ሁለት .................................................................................................................12**

*የኦዲት ግኝቶች* --------------------------------------------------------------------------------- 12

*ከፍላጐት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦት ስለመኖሩ* .......................................12
*ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ የመኖ ባንኮች ስለመኖራቸው*................................................................15
*ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊነት የመተካት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ*..............................16
*ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረም የማስወገድ ና የማልማት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ* .............21
*በግጦሽ ሥፍራዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ስለመኖሩ* .................23
*የዳልጋ ከብት ጤና አገልግሎት ስለመዳረሱ ና አጥጋቢ ስለመሆኑ* ........................................28
*የአገር ውስጥ የዳልጋ ከብት ዝርያ የማሻሻያ ተግባርን በተመለከተ* .........................................34
*ለሞያተኞችና ለአርብቶ አደሮች የሚሰጥ የግንዛቤ ማዳበሪያና ሥልጠና ስለመኖሩ*.......................35
*በ ንስሳት ሐብት ልማት ዙሪያ ብሔራዊ የጋራ ጉባኤ ስለመኖሩ*.................................................40
*በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ የመረጃ ሥርዓት ስለመኖሩ*......................................................44

**ክፍል ሶስት .................................................................................................................46**

*የማሻሻያ ሃሳቦች*------------------------------------------------------------------------------ 46

*ከፍላጐት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦትን በተመለከተ* ....................................46
*ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ የመኖ ባንኮች ስለመኖራቸው* ...............................................................46
*ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊነት የመተካት ሥርዓትን በተመለከተ* ...............................46
*ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረም የማስወገድ ና የማልማት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ* .............47
*በግጦሽ ሥፍራዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ* ............47
*የዳልጋ ከብቶች ጤና አገልግሎት ስለመዳረሱ ና አጥጋቢ ስለመሆኑ* .......................................48
*የአገር ውስጥ የዳልጋ ከብት ዝርያ የማሻሻያ ተግባርን በተመለከተ* .........................................48
*ለሞያተኞችና ለአርብቶ አደሮች የሚሰጥ የግንዛቤ ማዳበሪያና ስልጠናን በተመለከተ*......................48
*በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ብሔራዊ የጋራ ጉባኤ ስለመኖሩ*.................................................49
*በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ የመረጃ ስርዓት ስለመኖሩ* .......................................................49

# ክፍል አንድ

## ማጠቃለያ /Summary/


1. ኢትዮጵያ በ ንስሳት ሀብት ሰፊ አቅም ያላት አገር መሆኗ ጥናቶች ያሳያሉ:: በማዕከላዊ ስ ትስቲክስ ኤጀንሲ የ2001 ዓ.ም ሪፖርት መሠረት በሀገሪቱ 49.3 ሚሊዮን የዳልጋ ከብቶች መኖራቸው ውቋል:: የዳልጋ ከብት 85 በመቶ የሚሆነውን የወተት ምርት የሚሸፍን ቢሆንም በሀገሪቱ ካለው የከብት ሀብት ብዛት አንፃር ሲ ይ የወተት ምርቱ አነስተኛ ነው::
2. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በዋነኝነት በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ላይ የሚከናወኑ ተግባራት ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑ ና የተያዘለት አላማው ስኬ ማ መሆኑን የማጣራት፣ የአሰራር ችግሮችን በመፈተሽ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው::
3. ኦዲቱ በሁለት የኦዲት ጭብጦች ላይ በመመርኮዝ የክዋኔ ኦዲት ሥራው ተከናውኗል:: አንደኛው ጭብጥ ከመኖ ና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የዝርያ ማሻሻል፣ ምር ማነት ና በመጠን የማሳደግ ንዲሁም የግንዛቤ ማዳበርና የመረጃ አያያዝ ተግባራት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ በከብት ሐብት ልማት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት፤ የምርምር ውጤቶችንና ዘመናዊ የከብት ርባ ዘዴዎችን ለሕብረተሰቡ የማድረስ ተግባራት ጋር የተገናኘ ነው::
4. ነዚህን የኦዲት ጭብጦች ለማጣራት 44 የኦዲት መስፈርቶች ተዘጋጅተው ጉዳዩ የሚመለከተው የግብርና ሚኒስቴር አስተያየት ንዲሰጥበት ተደርጓል::
5. በኦዲቱ ወቅት ከተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ውስጥ ከፍላጎት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦት አለመኖር ነው:: በኦሮሚያና በአማራ ብሔራዊ ክልሎች በመስክ ጉብኝት ከተከናወነው ና ከሌሎቹ ክልሎች ጋር በደብዳቤ ልውውጥ በተገኘው መረጃ መሠረት የመኖ ዘርና ዕዋት ሥርጭት በየአካባቢው ካለው ፍላጎት በ ጅጉ ያነሰና የሰብል ተረፈ ምርት የማቀነባበርና ለገበያ የማቅረብ ሥርዓት ያልተዘረጋ ሆኖ ተገኝቷል::
6. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ 500 የመኖ ባንኮችን በአደጋ ጊዜ የዳልጋ ከብቶችን ለተወሰነ ጊዜ ለመመገብ ንዲያስችል ከ1999-2003 ዓ.ም በ ስትራቴጂክ ቅድ የያዘ ቢሆንም ተግባራዊ የሆነው በ ስትራቴጂ ከተያዘው በሶማሌና አፋር ክልሎች 21 የሚሆኑ ባንኮች ብቻ መሆኑ ውቋል::
7. ልቅ ግጦሽን ለመቆጣጠርና በዘመናዊ ሥርዓት ለመተካት የሚያስችል ሥራ ያልተከናወነ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህ ረገድ በትግራይ ክልል 427,517 ሄክ ር መሬት

ተከልሎ የአፈርና የውሃ ቀባ ለግጦሽ መሬት ዝግጅት መደረጉ መልካም ጅማሬ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

8. ይሁን ንጂ በብዙ ቦ ዎች የ የው ልቅ ግጦሽ የመኖ ብክለትን የሚያስከትል፤ በሽ ን ለማስፋፋት አመቺ ሁኔ ን የሚፈጥር፤ የመኖ ዝርያ ንዲመናመንና ንዲጠፉ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የተፈጥሮ ሀብት ና ብዝሀ ሕይወት ጥበቃን የሚያደናቅፍ ፈርጀ ብዙ ችግሮችን የሚያስከትል ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የግጦሽ መሬቱ በበርካ ቦ ዎች ላይ በቁጥቋጦዎችና በአላስፈላጊ አረሞች ተሞልቶ ይቷል፡፡

9. የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሻሻለ የግጦሽ መሬትን በ40 በመቶ ለማሳደግ የያዘው ዕቅድ ግብ ንዳይመ በማድረግ በመኖ ጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የዳልጋ ከብት ምር ማነት መቀነስን ለመግ ት የሚደረገውን ጥረት ውጤ ማ ንዳይሆን አድርጎ ል፡፡

10. ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በ ያንዳንዱ ቦ የ የ ዋነኛ ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከሁለት ቀበሌዎች ማለትም በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ከሚገኙት ሐሮበኬ ቀበሌና ቆማሐራ ቀበሌ በስተቀር በመስክ ጉብኝት ወቅት በ ዩትና በደብዳቤ ልውውጥ ከተገኙ መረጃዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አይነተኛ ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የውሃ ማከማቻ ኩሬ ባለባቸው ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ቀበሌዎች ንኳን ተገቢው ጥንቃቄ የማይደረግ በመሆኑ የበሽ አምጭ ተዋህስያን መራቢያ ና የአፈር ደለል መከማቻ ንዲሆን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በጥቅሉ በመስክ ጉብኝት በ ዩት ቦ ዎች የከብቶች መሰማሪያ የግጦሽ ሥፍራዎች ዳልጋ ከብቶች የሚጠጡት ከወራጅ ወንዞች ውሃ ሲሆን ወንዞቹም ለልብስ ና ለገላ መ ጠቢያነት የሚውሉ ከመሆናቸውም በላይ ለተሽከርካሪዎች የ ጥበት አገልግሎት የሚውሉ መሆናቸው ተስተውሏል፡፡

11. የዳልጋ ከብት ጤና አገልግሎት መደበኛ የክትባት አገልግሎቱም ሆነ የህክምና አገልግሎቱ አጥጋቢ በቂ አለመሆኑ ተስተውሏል፡፡ በዚህ ሳቢያ የዳልጋ ከብቶች በበሽ ንዳይያዙ ና ንዳይሞቱ መከላከል ሲቻል ከብቶች ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ሞተዋል፡፡ ይኸውም በቦረና ዞን ከግንቦት-ሐምሌ 2002 ዓ.ም ድረስ ብቻ የክትባት አገልግሎት በወቅቱ ባለመስጠቱ 4562 የዳልጋ ከብቶች መሞ ቸው ውቋል፡፡ ይህ የአንድ ጊዜ ክስተት ብቻ ሳይሆን መጠኑ ይለያይ ንጂ በአካባቢው በየዓመቱ የዚህ ዓይነት ችግር መኖሩ ውቋል፡፡ የሕክምና ክሊኒኮችም የባለሙያ ጥረት፣ የመድሀኒት አቅርቦት ማነስ ና በሕክምና መሣሪያዎች ካለመሟላት በተጨማሪ የሕክምና መስጫ አገልግሎት/ክሊኒኮች/ በተፈለገው ቦ አለመገኘት ተጠቃሽ ችግር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

12. ምንም ንኳን በሀገር ውስጥ በሥጋ ምር ቸው የተሻለ ምርት በሚሰጡት ላይ ጥናት ተደርጎ በደረጃ የቦረና፣ የፎገራ፣ የከረዩ የመሳሰሉት ጥሩ ምርት መስጠት

ንደሚችሉ ቢ ወቅም በሥጋ ምርት ዙሪያ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ግን ያልተጀመረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

13. ለሞያተኞች ና ለአርብቶአደሮች የሞያ ማሻሻያ ና የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና በተለያዩ ክልሎች መኖራቸው የሚበረ ቢሆንም ጅግ አነስተኛ የሆነና የመነሻ ጥናትን መሰረት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ሥልጠናው ያመጣውን ውጤት ለመገምገም የሚያስችል ስልት የሌለው አሠራር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

14. የ ንስሳት ሀብት ልማቱን ለማፋጠንና ከዘርፉ የሚጠበቀውን ጥቅም ውን ለማድረግ የፌዴራልና የክልል መስሪያ ቤቶችን ንዲሁም ባለድርሻ አካላትን በመደበኛነት የሚያገናኝ የጋራ የምክክር መድረክ መኖሩ ጅግ አስፈላጊ መሆኑ ይ መናል፡፡ ይሁንና ይህ ዓይነቱ መድረክ ያልተመሰረተ መሆኑ ውቋል፡፡ ነገር ግን በ1998 ዓ.ም የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል የተቋቋመ ቢሆንም ካውንስሉ ሁሉንም የግብርና ዘርፍ በሚዳስሱ ጉይዮች ላይ የሚመክር በመሆኑ የ ንስሳት ሀብት ልማት ላይ ጊዜ ወስዶ ና ትኩረት ሰጥቶ በጥልቀት ለመወያየትና ችግሮችን ለመለየት፣ የመፍትሄ ርምጃ ለመውሰድ፣ የዘርፉን አስተዋፅኦ ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ና ስልቶችና ስትራቴጂዎችን ለመለየት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

15. አስተማማኝ፣ ወቅ ዊና በተዋረድ የሚመጣ የመረጃ ፍሰት ትክክለኛ ወቅ ዊ ሁኔ ዎችን የሚያሳይ ከመሆኑም ባሻገር በመስኩ የሚነሱ ችግሮችን በተገቢው ጊዜ መፍትሄ ለመስጠት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ንደሆነ ይ መናል፡፡ ይሁን ንጂ በወረዳ ደረጃም ይሁን በክልል ቢሮዎችና በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከ ንስሳት ሀብት ልማት ጋር በተያያዘ መረጃ የሚጠናከርበት፣ ልውውጥ የሚደረግበትና ለተጠቃሚዎች ዝግጁ የሚሆንበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ ውቋል፡፡

16. ከላይ በአጭሩ የተገለፁት ግኝቶች የሚያመለክቱት ከ ንስሳት ሀብት ልማቱ ተገቢውን የማህበራዊ ና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ውን ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱን ነው፡፡

17. የኦዲት ግኝቶቹን መሠረት በማድረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦትን ለማሻሻል፣ የመኖ ዘር ማሰራጫ ጣቢያ ማቋቋም፤ የመኖ አምራች ማህበራትን ማደራጀትና ድጋፍ መስጠት፤ የተፈጥሮ ግጦሽን መንከባከብና ማልማት፣ የተሻሻሉ መኖዎችን በስፋት ማምረት ና የመኖ ዘር ማባዛትና ማሰራጨት ተግባራት የሚያካትት ቅድ ሊኖረው ና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

18. የጋራ/የወል/ ልቅ ግጦሽን በዘመናዊ የግጦሽ ሥርዓት በመተካት በተለይ የግጦሽ መሬት አስተዳደር መመሪያ በአስቸኳይ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ሁሉ ከማሰራጨት አልፎ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡

19. የንፁህ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያለበት ከመሆኑም ባሻገር አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩ ተሣ ፊ ና ተጠያቂነት የሰፈነበት

አሰራር ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ የንፁህ ውሃ አቅርቦት በሌለበት የወንዝ ውሃን የሚጠጡ ንስሳትን ከአደጋ ለመጠበቅ በወንዞች ውስጥ የልብስ፣ ገላ ና ተሽከርካሪ ጥበት ንዳይከናወን ክትትል ና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

20. የዳልጋ ከብቶችን ጤና ለመጠበቅ የጤና ተቋማት በሙሉ በአቅማቸው ንዲሰሩ ማድረግ፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ ለየአካባቢው አስፈላጊ የሆኑ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት በተገቢው መንገድ ተሟልተው የሚገኙበት ሁኔ ሊመቻች ይገባል፡፡ በሀገሪቱ የሚከሰቱ በሽ ዎችን መለየት መከላከል መቆጣጠር ተግባርም በአስቸኳይ ሊተገበር ይገባል፡፡

21. በ ንስሳት ሀብት ልማት ላይ የሚመክር ብሔራዊ የጋራ የምክክር መድረክ በመስኩ ያለውን ችግር ለመለየትና መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ጥናት ተጠንቶ መፍትሄ ሊደረግለት ይገባል፡፡

22. የመረጃ ስርዓቱን የመዘርጋት ተግባር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአስቸኳይ ሊደራጅና ለአገልግሎት ሊውል ይገባል፡፡

## መግቢያ

23. በኢትዮጵያ ሪክ ውስጥ የግብርናን ሥራ በበላይነት የሚመራ ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በ1900 ዓ.ም. ሲሆን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ሥርዓቶች የተለያየ ስያሜ የተሰጣቸው አካላት ክፍለ ኢኮኖሚውን ሲመሩ ቆይተዋል፡፡

24. በኢፌዴሪ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ በተሰጠው ልዩ ትኩረት በ1984 ዓ.ም. የግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተነድፎ በተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ክፍለ ኢኮኖሚው በገበያ ንዲመራ በማድረግ፤ ምርትና ምር ማነት በመጠንና በጥራት በማሳደግና ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በማምጣት ህዝቡን ከድህነት የማላቀቅ ተግባር በተሻለ ሁኔ ለመፈፀም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል ባወጣው አዋጅ ቁጥር 380/96 መሰረት ቀደም ሲል ራሳቸውን ችለው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ሁለት ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ሌሎች አራት ድርጅቶች በአንድ ላይ ተዋህደው ንዲደራጁ በማድረግ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

25. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግብርና ልማት ዘርፍ የሚካተቱትን የደን፤ የ ጽዋት፤ የአዝዕርትና ርሻ ንዲሁም የ ንስሳት ሀብት ና ተዛማች ቴክኖሎጂዎች ያጠቃለለ ስራ ያከናውናል፡፡

26. ኢትዮጵያ በ ንስሳት ሀብት ሰፊ አቅም ያላት አገር ናት፡፡ በማዕከላዊ ስ ትስቲክስ ኤጀንሲ በ2001 ዓ.ም በተደረገ ጥናት 49.3 ሚሊዮን የዳልጋ ከብቶች፤ 25 ሚሊዮን በጎች፤ 22 ሚሊዮን ፍየሎች፤ 1.78 ሚሊዮን ፈረሶች፤ 5.42 ሚሊዮን አህዮች፤ 0.37 ሚሊዮን በቅሎዎች፤ 38 ሚሊዮን ዶሮዎች፤ 5 ሚሊዮን የንብ ቀፎዎች በሀገሪቷ መኖሩን ይገልፃል፡፡ የተጠቀሰው አሀዝ ሀገሪቱ በ ንስሳት ሀብት ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም አስረኛ ደረጃን ይዛ ንደምትገኝ ይጠቁማል፡፡

27. ሀገሪቱ በ2002 በጀት ዓመት ከቁም ንስሳትና ከሥጋ የወጭ ንግድ 125 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ አግኝ ለች፡፡ ከ1997 ስከ 2002 ዓ.ም ባሉት ስድስት ዓመ ትም የሀገሪቱ የሥጋና የቁም ንስሳት ወጭ ንግድ በአማካኝ በዓመት 20 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡ በነኚህም ዓመ ት 445 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን የሪፖርተር አማርኛ ጋዜጣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ዋቢ በማድረግ ረቡዕ ነሐሴ 12 ቀን 2002 ዓ.ም ለንባብ አብቅቷል፡፡

28. የፈጣንና ዘላቂነት ያለው እድገት ለማስፈን ድህነትን የማስወገድ እቅድ (PASDEP) የ2002 የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት የእቅድ ክንውን ሪፖርት እንደሚያመለክተው በሀገሪቱ ከሚገኘው ጠቅላላ የወተት ምርት 85 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍነው የዳልጋ ከብት ወተት ነው፡፡ ካለውም የዳልጋ ከብት የወተት ምርት 97 በመቶ የሚገኘው ከሀገር በቀል ዝርያ ካላቸው የዳልጋ ከብቶች ሲሆን ከተሻሻሉ ዝርያዎች

የሚገኘው የወተት ምርት 3 በመቶ አይበልጥም:: በሀገሪቱ ካለው የከብት ሀብት ብዛት ጋር ሲነፃፀር የወተት ምርቱ በጣም አነስተኛ በመሆኑ የአንድ ሰው ዓመ ዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው::

## የግብርና ሚኒስቴር ራዕይና ተልዕኮ

29. የሚኒስቴር መ/ቤቱም ራዕይ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም የዳበረ በገበያ የሚመራ ግብርና ሥርዓት ተገንብቶ ከድህነት የተላቀቀ ህብረተሰብ ተፈጥሮ ማየት ነው:: ተልዕኮውም የህብረተሰቡን አስተሳሰብና አመለካከት በመለወጥ ኋላ ቀር ከሆነ የአስተራረስና የ ንስሳት አረባብ ዘዴ በማላቀቅ የሰው ይል ምር ማነትን በማሳደግ የአካባቢንና የተፈጥሮ ሀብትን በመንከባከብና በዘላቂነት ጥቅም ላይ በማዋል በምርምር የተደገፈ የተሻሻለ ቴክኖሎጂን ለአርሶ አደሩ፤ አርብቶ አደሩ፤ ከፊል አርብቶ አደሩና ለግል ባለሀብቱ በማላመድና በማስተዋወቅ መልካም አስተዳደር የሰፈነበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ብሎም ህብረተሰቡ ከድህነት ንዲላቀቅ ማድረግ ነው::

## የግብርና ሚኒስቴር ዓላማ፤ ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

30. የግብርናን አመራረት ወደ ገበያ ተኮር ያመራረት ስርዓት ማሸጋገርና የአርሶ አደሩን፤ የአርብቶ አደሩንና የከፊል አርብቶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋፅኦ ማድረግ፤ ስር ለሰደደ የምግብ ጥረት ተጋላጭ ለሆነው የሕብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤ የተፈጥሮ ሀብ ችንን በመንከባከብና በአግባቡ በመጠቀም ለግብርና ልማ ችን የሚኖረውን አስተዋፅኦ ማሳደግ ነው::

### ሥልጣንና ተግባር:-

- የምግብ ዋስትና ፕሮግራምን መምራትና ማስተባበር፤
- ለገበሬዎችና ለአርብቶ አደሮች የሚሰጡ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ንዲስፋፉ ማበረ ትና፤ ድጋፍ መስጠት፤
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎቶች ለገበሬዎችና ለአርብቶ አደሮች የሚቀርቡበትን ሁኔ ማመቻቸት፤
- በግብርና መስክ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የተሟላ ድጋፍ መስጠት፤
- በግብርና ልማት ላይ ተፅዕኖ የሚኖራቸውን ወቅ ዊ ሁኔ ዎች መከ ተልና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት መዘርጋት፤
- ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆኑ ከሀገር በሚወጡ ዕፅዋት፤ አዝርዕት፤ ንስሳትና የ ንስሳት ተዋፅኦ ላይ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር ማድረግ፤

- የ ንስሳትና የዕፅዋት በሽ ዎች ወረርሽኝንና ተዛማች ተባዮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊውን ርምጃ መውሰድ፤
- የግብርና ልማት በገበያ ንዲመራና ቀልጣፋ የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት ስርዓት ንዲፈጠር ለማድረግ ገበሬዎች፤ አርብቶ አደሮችና በግብርና ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶች የዓለም ገበያን በቅርብ የተከ ተለ የተሟላ፤ ወቅ ዊና ትክክለኛ የገበያ መረጃ ንዲያገኙ ማድረግና የዋና ዋና የግብርና ምርቶችና ግብዓቶች የገበያ ትንበያ ጥናት አካሂዶ ለሚመለከ ቸው አካላት ማሰራጨት፤
- የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ተቋሞችንና ማዕከሎችን ማቋቋምና መምራት፤

ከሚጠቀሱት ዋናዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት

31. የግብርና ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በአራት ዋና ዋና የስራ ዘርፎች (ግብርና ልማት ዘርፍ፣ የግብርና ግብይት ዘርፍ፣ የተፈጥሮ ሃብት ዘርፍ ና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ) ና በስምንት ድጋፍ ሰጪ የስራ ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የ ንስሳት ልማት ስራው በግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ስር በኬዝ ቲም የተዋቀረ ነው፡፡

## የሰው ሃይል

32. የግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት በ2002 በጀት ዓመት የነበሩት የሰራተኞች ብዛት በአጠቃላይ 1227 ናቸው፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

33. የግብርና ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ ከመንግስት በሚመደብ በጀት የሚተዳደር ሲሆን፡-
    - በ2000 በጀት ዓመት ለመደበኛ በጀት ብር 98.85 ሚሊዮን ተመድቦ ብር 79.89 ሚሊዮን ወጪ ሲሆን
    - በ2001 በጀት አመት ደግሞ ለመደበኛ በጀት ብር 139.81 ሚሊዮን ሲመደብ ብር 119.00 ሚሊዮን ወጪ ሆኗል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

34. የግብርና ሚኒስቴር በብሔራዊ የ ንስሳት ሃብት በዳልጋ ከብት ሃብት ልማት ላይ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በመመርመር ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑና

ወጪውም ቁጠባን ያገናዘበና አላማውንም ስኬ ማ ማድረጉን በማጣራት የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳቦችን (Recommendations) ለመስጠት ነው::

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና ጭብጦች

**35.** ብሔራዊ የ ንስሳት ሐብት የዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን በሁለት የኦዲት ጭብጦች (Issues) በመክፈል ዝርዝር የክዋኔ ኦዲት ሥራው ተከናውኗል:: ሁለቱ የኦዲት ጭብጦችም:-

1. ለዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚከናወነው የመኖ ና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የዝርያ ማሻሻል፣ ምር ማነት ና በመጠን የማሳደግ ንዲሁም የግንዛቤ ማዳበርና የመረጃ አያያዝ ተግባራት ብቃት ባለው መንገድ የሚከናወኑና ስኬ ማ መሆናቸውን ማጣራት፤

   የሚል ሲሆን ይህም በ3 ንዑስ የኦዲት ጭብጦች ተከፍሏል::

   1.1 የዳልጋ ከብት ምር ማነትን ለማሳደግ የሚያስችል የመኖ፤ ግጦሽ መሬትና ውሃ አቅርቦት፤ ንዲሁም የዝርያ ማሻሻል ተግባራት በብቃት የሚከናወኑ ና ስኬ ማ መሆናቸውን ማጣራት፤

   1.2 የዳልጋ ከብቶች የግጦሽ አካባቢና መኖሪያ ስፍራ ጤናማ የማድረግ ስራ የሚከናወን፤ የሕክምና አገልግሎት ና የመድሐኒት አቅርቦት የተሟላ መሆኑን ማጣራት፤

   1.3 የዳልጋ ከብቶች ምር ማነትና ብዛትን ለመከ ተል የሚያስችል የክትትልና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱንና በከብት ርባ ና ተዛማጅ ሥራ ላይ ለተሰማራው ሕብረተሰብ የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የሚሰጥበት ስርዓት መኖሩንና ተፈፃሚ መደረጉን ማጣራት፤

2. በከብት ሐብት ልማት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት፤ የምርምር ውጤቶችንና ዘመናዊ የከብት ርባ ዘዴዎችን ለሕብረተሰቡ ለማድረስ የሚያስችል ስርዓት ስለመዘርጋቱና ስኬ ማ ስለመሆኑ ማጣራት፤የሚሉ ናቸው::

## የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/

**36.** ለተመረጡት ሁለት የኦዲት ጭብጦች 43 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ በቅድሚያ አስተያየት ንዲሰጥበት ጉዳዩ ለሚመለከተው የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ተልኮ አስተያየት ተሰጥቶበ ል:: የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዟል::

## የኦዲቱ ወሰን ና ዘዴ/ሥልት/

37. የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2000-2001 ዓ.ም ያለውን ሁለት የበጀት አመ ት ነው:: ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) መሠረት ነው:: ለክዋኔ ኦዲቱ በተዘጋጁት የመመዘኛ መሥፈርቶች መሠረት መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል:: ንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው ላፊዎችና ሠራተኞች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል::

38. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በግብርና ሚኒስቴር በግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ሲሆን ከ ንስሳትና ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፤ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግሥት የእንስሳት ጤናና ገበያ ኤጀንሲ፤ ከአማራ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፤ ከኢትዮጵያ የእንስሳት መኖ ኢንዱስትሪ ማህበር ንዲሁም ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በቃለ መጠይቅና ዶክመንት ክለሳ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል:: ከፍተኛ የዳልጋ ከብት ሃብት ከሚገኙባቸው ክልሎች መካከል በናሙና በተመረጡ ኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሰሜን ሸዋ ዞን /ግራር ጃርሶ ወረዳ፤ ደ/ሊባኖስ ወረዳ፤ ውጫሌ ወረዳ፤ ቅምብቢት ወረዳ፤ አሌልቱ ወረዳ/፤ ምስራቅ ሸዋ ዞን /መቂ እና ዝዋይ/ ምዕራብ አርሲ ዞን /ላንጋኖ/ አካባቢዎች፤ ቦረና ዞን/ ያቤሎ፤ ቡሌ ሆራና አባያ ወረዳዎች/፤ ንዲሁም አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በህርዳር ዙሪያ ወረዳ ና በሰሜን ሸዋ ዞን ባሶና ወራና ወረዳ የመሥክ ሥራ በማከናወን የኦዲት ሥራው ተሰርቷል::

39. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በስተቀር ለተቀሩት ክልሎች መጠይቆች የተላከ ሲሆን ይህ ሪፖርት ስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ከሁለቱ ክልሎች(ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና ከሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ) በስተቀር መልስ ልከዋል::

## የአሰራር ሂደት መግለጫ (Process Description)

### የግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ያለው የሥራ ሂደት:-

40. በግብርና ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት የቴክኖሎጂ ሽግግር ኬዝ ቲም የእንስሳትን ምርት ዕድገት ንዲፋጠን አዋጭ፣ አማራጭና ውጤ ማ የ ንስሳት ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎችን ያስፋፋል፣ ተገልጋዩንም ተጠቃሚ ያደርጋል:: የ ንስሳት ምርትና ምር ማነት በላቀ ደረጃ ንዲያድግ በ ንስሳት ምቅ ሀብትና ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ላይ በክልሎች የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል::

41. የ ንስሳት ውጤቶችን ምርትና ምር ማነት በመጠንና በጥራት ለማሳደግ የሚረዱ አዋጭ አማራጭና ውጤ ማ የ ንስሳት ቴክኖሎጂ ፖኬጆችን ያዘጋጃል፤ ስልጠና ይሰጣል፤ ውጤ ማ ቴክኖሎጂዎችን ያስፋፋል:: ከዚሁ ጋር በማያያዝ የ ንስሳት ሀብት ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ በችግሮች መፍትሄ ፍለጋ ላይ ይሳተፋል፤ ስልጠና ይሰጣል:: በ ንስሳት ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን ከየክልሎች ያሰባስባል፣ ይቀምራል፣ ወደተግባር ንዲሸጋገርም ለየክልሎቹ ይልካል፣ ተሞክሮዎቹ መስፋፋ ቸውን ይከ ተላል፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦችን ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመነጫል፣ የፀደቁትን ፖሊሲዎችና ደንቦች ለ ንስሳት አርቢው ህብረተሰብ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣ በሥራ ላይ ንዲውል ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል::

42. የልማት አካላት ግንኙነት በእንስሳት ሀብት ልማት የህብረተሰቡ ችግሮችና ፍላጐት ለማሟላት ንዲቻል የአገር አቀፍ የልማት አካላት ካውንስል ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ለየባለድርሻዎቹ የሥራ ክፍፍል በመለየትና የሥራ ድርሻዎችን በማሳወቅ አፈፃፀሙን ይከ ተላል፤ የተለያዩ የልማት አካላት ባለድርሻዎችን በጋራ በመተባበር ለሀገር ዕድገት የሚሰሩበትን ሁኔ ያመቻቻል፤ ከየክልሎች ከምርምር ተቋማት ጋር በመሆን የቴክኖሎጂ ቅድመ ስርጭት ሙከራዎችን የመስክ ጉብኝት ኘሮግራም ያስተባብራል፣ በመስክ በመገኘት በግምገማው ላይ ይሣተፋል፣ የተገኙ አመርቂ ተሞክሮዎችንም ለማስፋፋት ና አገልግሎት ንዲውሉ መረጃውን ለቴክኖሎጂ ሽግግር ኬዝ ቲም ያቀርባል::

43. ከዚሁ ጋር በማያያዝ በየደረጃው የ ንስሳት የምርምር ማዕከላት የኤክስቴንሽንና የአርሶ አደሩ፤ አርብቶ አደሩ ና ከፊል አርብቶ አደሩን አማካሪ ኮሚቴዎች ንቅስቃሴ ላይ ግምገማ ያደርጋል:: ንዲሁም በየደረጃው ለተመሠረቱ የምርምር ማዕከላት ኤክስቴንሽንና አማካሪ ኮሚቴዎች ንዲጠናከሩና ባልተመሠረተባቸው

አካባቢዎች ንዲመሠረቱ በማድረግ በግምገማው ወቅት የ ዩትን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመለየት ለግብዓትነት ለካውንስሉ አጠቃላይ ስብሰባ ያቀርባል፡፡

44. በሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ የግብርና ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር አስፈላጊ የሰለጠነ የሰው ይል ደረጃ በደረጃ ንዲሟላ ያደርጋል፡፡ ባለሀብቱን፣ አርሶአደሩን፣ አርብቶአደሩንና ከፊል አርብቶ አደሩን የሚያስተሳስርና የሀገሪቱን የ ንስሳት ልማት የሚያግዙ የአጭር የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅድና የሥራ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን ከሚመለከ ቸው ጋር በመተባበር ንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀማቸውን በመከ ተል ቴክኒካዊ ገዛ ይሰጣል፡፡

## <u>የ ንስሳትና ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት</u>

45. የ ንስሳት ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የኳራንቲንና ኢንስፔክሽን አገልግሎት ይሰጣል፤ የጥራት ቁጥጥር ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡም ሆነ ከሀገር በሚወጡ ንስሳት አማካኝነት የ ንስሳት በሽ ስርጭት ንዳይኖር የመከላከል ስራ ማከናወን ና ወደውጪ ለሚላኩ የቁም ንስሳትና የ ንስሳት ውጤቶች ዓለም አቀፍ የጤና ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣል፡፡ የስራ ንቅስቃሴውንም በሪፖርት ለግብርና ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### I. ለዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚከናወነው የመኖ፣ ውሃ ና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የግንዛቤ መዳበርና ሥልጠናን በተመለከተ:-

#### ከፍላጐት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦት ስለመኖሩ

46. የ ንስሳት ሀብት ልማትን ለማፋጠንና ምር ማነትን ለማሳደግ ንዲያስችል የተመጣጠነ የከብት መኖ አቅርቦት በየትኛውም ፍላጐት ባለበት አካባቢ መሟላት ይኖርበ ል፡፡ ይህንንም ውን ለማድረግ ንደየአካባቢው አመቺነት የተሻሉ የመኖ ፅዋት የማልማት፤ የማባዛትና የማሰራጨት ንዲሁም የሰብል ተረፈ ምርቶችን በማቀነባበር የሚመረቱበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

47. በኦዲቱ በተመለከትናቸው በኦሮሚያ ና በአማራ ብሔራዊ ክልሎች የመኖ ዘርና ፅዋት ሥርጭት በየአካባቢው ካለው ፍላጐት በ ጅጉ ያነሰና የሰብል ተረፈ ምርት የማቀነባበርና ለገበያ የማቅረብ ሥርዓትም ያልተዘረጋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በደብዳቤ መጠይቅ ላደረግንላቸው ሌሎች ክልሎችም /ትግራይ፣ አፋር፣ ደቡብ ሕዝቦች ብሔሮችና ብሔረሰቦች፣ ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ ና ሐረሪ/ በ ንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ላይ ዋነኛ ችግር ተብሎ የሚጠቀሰው የመኖ አቅርቦት ጥረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

48. በተጨማሪም በፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል አምስተኛና ስድስተኛ አመ ዊ ስብሰባዎች በተደረጉባቸው አመ ት /ነሐሴ 29/2001 ና ሚያዝያ 14-15/2002 ዓ.ም በቅደም ተከተሉ/ የ ንስሳት ሐብት ልማቱ ዋነኛ ችግር የመኖ ጥረት መሆኑ በአጀንዳነት ተነስቷል፡፡

49. በየወረዳዎችም በመዘዋወር ከግብርናና ገጠር ቢሮ ላፊዎችና ተወካዮች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ና የመስክ ጉብኝት ለመገንዘብ የተቻለው የመኖ ጥረት ዋነኛ ችግር መሆኑን ነው፡፡ ከመኖ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የተሰበሰበው መረጃ ከ ች በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 1: በየክልሉ ያለውን የመኖ አቅርቦት ሁኔ  የሚያሣይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ክልል | የመኖ አቅርቦት ጥረት/የተሟላ | የመኖ ማቀነባበሪያ አለ/የለም | ለመኖ አቅርቦት የተዘጋጀና ተግባራዊ የሆነ ስትራቴጂ አለ/የለም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | ጥረት | የለም | አለ |
| 2 | አፋር | ጥረት | የለም | አለ |
| 3 | አማራ | ጥረት | የለም | አለ |
| 4 | ኦሮሚያ | ጥረት | የለም | አለ |
| 5* | ቤኒሻንጉል | መልስ ያልሰጡ | መልስ ያልሰጡ | መልስ ያልሰጡ |
| 6 | ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች | ጥረት | የለም | አለ |
| 7 | ጋምቤላ | ጥረት | የለም | የለም |
| 8 | ሐረሪ | ጥረት | የለም | አለ |
| 9* | ሶማሌ | መልስ ያልሰጡ | መልስ ያልሰጡ | መልስ ያልሰጡ |
| 10 | ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር | ጥረት | የለም | የለም |

* ለቤንሻንጉል ጉምዝ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት  ና የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መጠይቆች የተላኩ ቢሆንም መልስ ያልሰጡ ናቸው::

**50.** ከላይ በሰንጠረዥ  ንደተመለከተው በሁሉም ክልሎች የመኖ  ጥረት መኖሩንና ችግሩን ለማቃለል የሚያስችል የመኖ ማቀነባበሪያ አለመቋቋሙን ነው:: ያለውን የመኖ  ጥረት ችግር ለማስወገድ ያልተቻለበትን ምክንያት  ንዲገልፁልን በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ለሚገኙት ከፍተኛ የ ንስሳት ሐብት ሞያተኛ ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፤ የመኖ ዘር በየክልሎቹ አለመኖርና ዘር የማባዛት ተሞክሮም አለመሥፋፋት፣ የመኖ ዘር አባዥ ድርጅቶች ውስን መሆኑ፣ በመንግሥት ደረጃም የመኖ ዘር ማባዣና ማሰራጫ ጣቢያ አለመኖር ዋነኛ ምክንያቶች  ንደሆኑ ገልፀዋል:: የአማራ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የግብርና ቴክኖሎጂ ብዜትና የግል ባለሀብት ድጋፍ ባለሙያም ቢሮውን በመወከል በሰጡት መልስ፤ በክልሉ ያለው የመኖ ፍላጐት 27 ሚሊዮን ቶን  ንደሆነና አቅርቦቱ ግን 18 ሚሊዮን /66.6%/ ብቻ በመሆኑ የ9 ሚሊዮን ቶን /33.3%/  ጥረት መኖሩንና ለዚህም ምክንያቱ የግጦሽ መሬት ማነስና የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች  ጥረት መሆኑን ገልፀዋል::

51. የኢትዮጵያ ንስሳት መኖ ኢንዱስትሪ ማህበር ሥራ አሥኪያጅም ስለዚሁ ጉዳይ ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፤ የተሻለ የመኖ ዘር ጥረት ዋነኛው ችግር ንደሆነና ለዚህ ጥረት በምክንያትነት የሚጠቀሰውም የግጦሽ መሬቶች ወደ ርሻነት የተቀየሩ የመሄድ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል::

52. ከኦዲቱ ውጤት ለመገንዘብ ንደተቻለው የመኖ ጥረት የ ንስሳት ሀብት ልማቱ /በ ንስሳት ጤንነት፣ የወተትና ሥጋ ልማት/ ንዳይስፋፋና ንዳያድግ ንቅፋት መሆኑን ነው:: የመኖ ጥረት ወደ ንስሳት ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች ንዳይበረ ቱ የሚያደርግ፣ የ ንስሳት ጤናን የሚያስተጓጉል፣ በሥጋና ወተት አቅርቦት ላይ ጥረት ንዲባባስ የሚያደርግ፣ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውንም የኢኮኖሚና ማህበራዊ /በሰው ጤንነት፣ ለዜጐች የገቢ ምንጭና የሥራ ድል፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ወዘተ/ ልማት የሚያስተጓጉል በመሆኑ ተፅ ኖው ፈርጀ ብዙ ና ከፍተኛ ነው::

53. ስለሆነም በ ኛ አስተያየት የመኖ ጥረት ችግርን ማስወገድ/ማቃለል ያልተቻለው በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ና በክልል የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮዎች አማካኝነት መከናወን የሚገባቸው ሥራዎች በበቂ ሁኔ አለመሰራ ቸው፣ ክትትልና የቁጥጥር ውሱንነትና የትኩረት ማነስ መሆናቸውን ከኦዲቱ ለመገንዘብ ችለናል:: ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ በኦሮሚያ የግጦሽ መሬት የነበሩት በ ርሻ መስፋፋት ምክንያት ወደ ርሻ መሬትነት የተቀየሩና በየጊዜው የዚህ አይነቱ ሁኔ የጨመረ መሄዱ የ ወቀ አማራጭ መፍትሄ አለመዘጋጀቱ፤ በአብዛኛው ክልሎች የመኖ አቅርቦትን ለማሻሻል የሚያስችል ስትራቴጂ ቢነደፍም ተግባራዊ አለመደረጉና በጋምቤላ ክልል ደግሞ ስትራቴጂ አለመነደፉ፣ የመኖ ማቀነባበሪያዎች ሊበራከቱ የሚችሉበት የድጋፍና የቅስቀሳ ሥራዎች የማይከናወኑ፤ ተራሮችንና ከፍተኛ ተዳፋትነት ያላቸውን ቦ ዎች በመከለል መኖ የማልማት ተሞክሮዎችን አለማስፋፋት፣ ልቅ የግጦሽ ሥርዓት አለመቆጣጠርና የ ንስሳት ቁጥርን በመቀነስ ምር ማነትን የማሳደግ ተግባር ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ ይጠቀሳሉ::

54. በአጠቃላይ በመላ ሐገሪቷ ያለውን የመኖ ፍላጐት ለማሟላት የሚያስችል ሁሉን አሳ ፊ፣ አጣዳፊ ና ቀጣይነት ያለው ርምጃ ካልተወሰደ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም በሚጠበቀው መጠን ማግኘት ካለማስቻሉ በላይ የ ንስሳት ሐብት ልማቱ በሐገሪቷ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ላይ የሚኖረውን አስተዋፅኦ ያስተጓጉላል:: ስለሆነም የ ንስሳት መኖ የሥነ-ምግብ ይዘትን ለማሻሻል የሚረዱ የሞላሰስ ማከማቻ ዲፖዎችን ለማቋቋም በዕቅድ የተያዘው ሥራ ተግባራዊ መሆን አለበት::

55. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ5 ዓመቱ/1999-2003/ ስትራቴጅክ ዕቅድም ሆነ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው ዕድገትን በማስፈን ድህነትን ማስወገድ ዕቅድ የሰብል ተረፈ

ምርቶችን የሥነ-ምግብ ይዘት ለማሻሻል የሚያስፈልግ የሞላሰስ ማከማቻ የሚሆን ያንዳንዳቸው መቶ ሺህ ሊትር የመያዝ አቅም ያላቸው 100 ዲፖዎችን ለማቋቋም በዕቅዱ ያካተተ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ መረጃዎችና የኦዲት ቡድኑ በአካል በጎበኛቸው በኦሮሚያና በአማራ ብሔራዊ ክልሎች የ ንስሳት መኖ ሥነ-ምግብ ይዘትን ለማሻሻል የሚረዱ የሞላሰስ ዲፖዎች አለመቋቋማቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም የመኖ ጥረት ባለበት ሁኔ ያለውንም የሰብል ተረፈ ምርት የሥነ- ምግብ ይዘት በማሻሻል መኖን በሚገባ መጠቀም ንዳይቻል በማድረግ የዳልጋ ከብት ምር ማነት ንዳያድግ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ የመኖ ባንኮች ስለመኖራቸው

56. በአደጋ ጊዜ የተወሰኑ የዳልጋ ከብቶችን ለተወሰነ ጊዜ መመገብ የሚችል የመኖ ባንኮችን በተወሰኑ መሬቶች በመኖ ንዲለሙ መደረግ ይኖርበ ል፡፡

57. ይሁን ንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአደጋ ጊዜ 250 ሺህ የዳልጋ ከብቶችን ለአንድ ወር ወይም 83 ሺህ የዳልጋ ከብቶችን ለ3 ወር መመገብ የሚችል 500 የመኖ ባንኮችን ያንዳንዳቸው ሁለት በሁለት ሄክ ር ስፋት ያላቸው መሬቶች በመኖ ንዲለሙ ለማድረግ በስትራቴጂክ ዕቅድ ያካተተ ቢሆንም፤ በኦዲቱ ወቅት የ ዩ መረጃዎችና ቡድኑ በአካል በጎበኛቸው ኦሮሚያና በአማራ ብሔራዊ ክልሎች በአደጋ ጊዜ የዳልጋ ከብቶችን ለተወሰነ ጊዜ መመገብ የሚያስችል የመኖ ባንኮች በመኖ ክምችት ንዲለሙ የማድረግ ተግባር ውስን መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ባለሙያ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ በሶማሌና አፋር ክልሎች ብቻ 21 የሚሆኑ የመኖ ባንኮች መኖራቸውንና ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ አለመሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህም በስትራቴጂክ ዕቅድ ከተያዘው በመቶኛ ሲሰላ 6.2 ይሆናል፡፡

58. የመኖ ባንኮች በስፋት ያልተቋቋሙበትን ምክንያት በግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ባለሙያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የበጀት ጥረት መኖር፤ ማከማቻ መጋዘን አለመኖር፣ የመኖ ባንኮች የተሰሩባቸው ቦ ዎች በግል የተያዙ መሆንና የህብረተሰቡ ግንዛቤ አናሳ መሆን የመሳሰሉ ችግሮች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ የበጀት ጥረትን በተመለከተ ችግሩን ለማሻሻል በፌዴራል ጉዳዮች አማካኝነት የሚተገበር የአለም ባንክ በሰጠው የፋይናንስ ምንጭ ንዲጠቀሙ የምክር አገልግሎት/ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር/ የተሰጠ ቢሆንም ምንም ለውጥ የሌለ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

59. የመኖ ጥረት ባለበት ሁኔ በተለይም በድርቅ ጊዜ የሚከሰተውን ችግር ለማሻሻል በስትራቴጂ የተያዘው ዕቅድ ተግባራዊ አለመሆኑ ለዳልጋ ከብቶች ምር ማነት ማነስ የራሱን አስተዋፅኦ በማድረግ ሀገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ ንዳትሆን አድርጓ ል፡፡

## ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊነት የመተካት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ

60. የግጦሽ መሬት አያያዝ፣ የመሬትን ለምነትና ምር ማነት ጠብቆ ለማቆየት፣ የዳልጋ ከብቶች ጤንነትንም ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ሊያዝ ይገባል፡፡ ይህንንም ውን ለማድረግ የግጦሽ መሬቱ ከብቶችን የመሸከም አቅም(carrying capacity) ሊወሰን፤ ንዲሁም ከሌሎች ንስሳትና የሰዎች ንቅስቃሴ ሊጠበቅና ሊከለል ይገባል፡፡ በቅደም ተከተልም አጭዶ የመመገብ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበ ል፡፡

61. ይሁን ንጂ በትግራይ ክልል ከተጀመረው ንቅስቃሴ በስተቀር በሌሎቹ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊ የግጦሽ አስተዳደር ሥርዓት የመተካት ሥራ አለመከናወኑ ውቋል፡፡ ለዚሁም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች በተመረጡና በዳልጋ ከብት ብዛት ርባ የ ወቁትን ወረዳዎች ባካተተ የመሥክ ሥራና ቃለ ምልልስ ንዲሁም ከሌሎቹ ክልሎች ጋር በደብዳቤ በተደረገ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራ ልቅ ግጦሽን ለመቆጣጠርና በዘመናዊ ሥርዓት ለመተካት የሚያስችል ሥራ ያልተከናወነ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

62. ዘመናዊ የግጦሽ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ በትግራይ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ አማካኝነት ጅምር ሥራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውንና መጠኑ 472,517 ሄክ ር መሬት በመከለል የአፈርና ውሃ ቀባ ለግጦሽ መሬት ዝግጅት መሆኑ በጥሩ ተሞክሮነት የሚጠቀስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በኦሮሚያ፤ በአማራ ና አፋር ክልሎች ውስን በሆኑ ቦ ዎች የመከለልና አጭዶ ለመመገብ ሙከራ መኖሩን ነገር ግን ከከብት ብዛቱና ከጅምር ሥራው አነስተኛነት ጋር ሲወዳደር ኢምንት ንደሆነ የቢሮ ተወካዮቹ ገልፀዋል፡፡

63. በመስክ ጉብኝት በተመለከትናቸው አካባቢዎች ሁሉ የዳልጋ ከብቶችም ሆኑ ልዩ ንክብካቤ የሚፈልጉ የወተት ላሞች ከሌሎች ከብቶች ንደ አህያ፤ በቅሎና ፈረስ ንዲሁም በግና ፍየሎች ጋር በአንድ የግጦሽ ሥፍራ ተደባልቀው የሚሰማሩ፣ የግጦሽ መሬቱም የመሸከም አቅሙ ሳይወሰንለት ከብት ያለው በሙሉ ክረምት ከበጋ አመቱን ሙሉ ያለገደብ በመልቀቅ የሚያስግጥ፣ የልጆች ኳስ መጫወቻ፣ ማንኛውም ሰው የሚተላለፍበትና ለመፀዳዳትም ከልካይ የሌለበት፣ አረም የበዛበትና ተግጦ በማለቁ አፈሩ የሚ ይበት፣ ከብቶችም ከፀሐይ ሊከለሉ የሚችሉበት ዛፍ የሌለበት፣ በቅርብ ርቀትም የመጠጥ ውሃና የሕክምና አገልግሎት የማይ ይበት፣ በአጠቃላይም ለ ንስሳት ሐብት ልማቱ ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ለማድረግ አዳጋች ሁኔ መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በአንዳንድ አካባቢም ለምሣሌ ግራር ጃርሶ ወረዳ፣ ዝዋይና መቂ አካባቢ የግጦሽ መሬት ባለመኖሩ ዳልጋ ከብቶች በመኪና መንገድ ዳርቻ ላይ የሚገኙ አረሞችን የሚመገቡ፤ በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ ለግጦሽ አመቺነት በሌላቸው ተዳፋት ቦ ዎችና ተራሮች ላይ የሚሰማሩ ሆኖ ተገኝቷል፡፡



ፎቶ 1: በኦሮሚያ ግራር ጃርሶ ወረዳ የዳልጋ ከብቶች ለግጦሽ በማይመች መሬት ላይ ተሰማርተው፡፡



ፎቶ 2: በኦሮሚያ መቂ አካባቢ ከብቶች በአስፋልት ዳር ለግጦሽ ተሰማርተው፡፡



ፎቶ 3፡ በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳ ከብቶች በተዳፋትና ለግጦሽ አመቺ ባልሆነ መሬት ላይ ተሰማርተው፡፡



ፎቶ 4፡ በኦሮሚያ ቦረና ዞን ሀሮ በኬ ቀበሌ የዳልጋ ከብቶች ልቅ ግጦሽ ላይ ተሰማርተው የሚያሳይ ፎቶ፡፡

**64. የግጦሽ መሬቶች ንዲከለሉና ንዲጠበቁ ባለመደረጉም የቆሻሻ መጣያ ንዲሁም በጐርፍ ውሃ በመሸርሸር ወደ ገደልነት**(Gully) **ተቀይረው ተገኝተዋል፡፡ ለምሣሌ**

በሰሜን ሸዋ ሰንዳፉ አካባቢ ካለው የአስፋልት መንገድ ግንባ ጋር ተያይዞ ከመሬት የሚወጣ አፈር በአካባቢው በሚገኘው የግጦሽ መሬት ላይ ንዲጣል መደረጉ፣ ዚሁ አካባቢ የሚገኝ የግጦሽ መሬትም በጐርፍ ምክንያት ተሰባብሮ(Gully erosion) ከግጦሽ መሬት ውጪ ንደሆነና የከብቶች ንቅስቃሴንም ንዳስተጓጐለ የሚጠቀስ ጉዳይ ነው:: በተጨማሪም የወተት ላሞች ለብቻቸው የግጦሽ መሬት ንዲኖራቸው አለመደረጉ፤ የዳልጋ ከብቶች በአጠቃላይም ከሌሎች ንስሳት ተለይተው ንዲሰማሩ የተደረገበት ሥፍራ አላገኘንም:: በተወሰኑ አካባቢዎችም ለግጦሽ አመቺነት ያላቸውና አመቱን ሙሉ መኖ ሊሰጡ የሚችሉ ርጥበት የማይለያቸውና በጣም ሰፊ መሬቶች ያሉ ቢሆንም በልቅ ግጦሽ መሬትነት የሚያገለግሉ ሆኖ ተገኝቷል:: ለምሳሌ በአማራ ክልል ደብረ ማርቆስ ዙሪያ ሣንተራ ቀበሌ ና ማቻክል ወረዳ ወላ ቀበሌ፤ በኦሮሚያ ፍቼ፤ ጫንጮና ሱሉል አካባቢዎች ተጠቃሽ ናቸው::



ፎቶ 5: በአማራ ክልል ደብረብርሃን አካባቢ ልቅ የግጦሽ ስርዓት የሚያሳይ የግጦሽ መሬት

65. የግል ዳልጋ ከብት ርባ ና ወተት ልማት ድርጅቶችን በተመለከተ፤ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የሚገኘው ጉደር ሰላሌ ወተት ልማት ንዲሁም ሰንዳፉ አካባቢ የሚገኘው ካሶ ቦረና የወተት ልማት ድርጅት በኦዲቱ የተዳሰሱ ሲሆን፣ የካሶ ቦረና ወተት ልማት ድርጅት ዘመናዊ የግጦሽ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ተጠቃሽ ሆኖ ተገኝቷል:: ይኸውም የግጦሽ መሬቱ የ ጠረና ከማንኛውም አላስፈላጊ ንክኪ የተጠበቀ፤ የከብቶቹ ቁጥርም ተመጥኖና አፈዙሮ የማስጋጥ ንዲሁም አጭዶ የመመገብ አሠራር ተግባራዊ የማድረግ፤ የመኖ ዘርን በማልማት የግጦሽ መሬት ለምነቱን ጠብቆ ምርት ንዲሰጥ የማድረግ፤ ከሐይለኛ ፀሐይ ለመጠለል የሚያስችሉ ዛፎች የተዘጋጁለት፤ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ከ50-200 ሜትር

ርቀት ውስጥ ንዲዘጋጅ የተደረገበት ሁኔ ተጠቃሽ ነው:: በዚህም ምክንያት ከብቶቹ የሚጠበቀውን የወተት ምርት ንደሚሰጡና በአጭር ጊዜ ንደሚደልቡ፤ በበሽ የመያዝ አጋጣሚውም ዝቅተኛና አማካኝ አመ ዊ የሞት መጠኑም ዜሮ/0%/ ንደሆነና በ3 ዓመ ት ጊዜ ውስጥ/ከ1999-2001/ አንድ ጥጃ ብቻ ንደሞተ ከድርጅቱ የሥራ መሪ ጋር ባደረግነው ቃለ ምልልስና በአካል ከተመለከትነው ሁኔ ለመረዳት ተችሏል::

66. ከልቅ ግጦሽ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው የሥራ ላፊዎች ጋር ቃለ ምልልስ ተደርጓል:: በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ሀብት ሞያተኛ በሰጡት መልስ፣ የዘመናዊ ግጦሽ መሬት አስተዳደር ግንዛቤና ክህሎት ማነስ፤ በኮሙኒቲ ደረጃ የግጦሽ መሬት አያያዝና አጠቃቀም ደንብ አለመኖርና የግጦሽ ማሻሻያ ሥርዓት ሥራዎች አለመተግበራቸው በምክንያትነት የሚጠቀሱ መሆኑን ገልፀዋል::

67. ለኦሮሚያ ክልል የ ንስሳት ሀብት ልማት ጤና ጥበቃና ገበያ ኤጀንሲ ተወካይና በየዘርፉ የሚገኙ ከፍተኛ ሞያተኞች በጋራ በሰጡት መልስ፤ ስለ ግጦሽ መሬት አያያዝና አጭዶ የመመገብ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ንደተጠናና ተግባራዊ ለማድረግ ንቅስቃሴ የተጀመረ መሆኑን ገልፀዋል::

68. ይሁን ንጂ ከዚህ ቀደም የተዘጋጁ ጥናቶች በአብዛኛው ተግባራዊ ባለመደረጋቸውና ስከ ዛሬ ስርዓቱ ባለመዘርጋቱ፣ የተሰጠው መልስ አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም:: ምክንያቱም ቀደምት የተዘጋጁና ተግባራዊ መደረግ የጀመሩ ዘመናዊ የግጦሽ መሬት አስተዳደር ና ዝርያ ማሻሻል ሥርዓት /ሻሸመኔ አካባቢ የነበረው የግጦሽ መሬት እና ዝርያ ማሻሻያ (አበርኖሳ) ይጠቀሳል/ መቅረቱና በሌላም አለመተካቱ የግጦሽ መሬት አስተዳደር ደንብ ስከዛሬ አለመውጣቱ፣ የሰርቶ ማሳያ ተግባራዊ ንቅስቃሴዎች አለመኖር፣ ለግጦሽ የሚውሉ መሬቶች ተለይተው አለመ ወቃቸው፣ ለዘርፉ የተሰጠው የትኩረት ማነስ መኖር ያመላክ ል:: የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ የክልል ቢሮዎች የግጦሽ መሬት ንዲሻሻልና በአግባቡ ጥቅም ላይ ንዲውል፤ የድርቆሽና ገፈራ ዝግጅት ሥርዓት መመሪያ የማዘጋጀትና የማሰራጨትን ንዲሁም ምርጥ ተሞክሮዎችን ንዲስፋፋ የማድረግ ላፊነቶች ያሉባቸው ሆኖ ሳለ በአግባቡ ተፈፃሚ አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም::

69. አሁን የሚስተዋለውን የልቅ ግጦሽ ሁኔ ለመቀየርና ዘመናዊ የግጦሽ መሬት ሥርዓት ተግባራዊ የሚሆንበትን አፋጣኝ ርምጃ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ሆነ የክልል ቢሮዎች በጋራ ና በተናጠል ስካልወሰዱ ድረስ፣ ሕብረተሰቡ ከ ንስሳት ተዋፅኦ የሚጠብቀውን ፍላጐት ለማሟላት የማያስችል፣ የግጦሽ መሬት ምር ማነት ንዲቀንስና ለአፈር መከላት በመዳረግ የመኖ ጥረት ንዲባባስ፣ የዳልጋ ከብቶችም

ለክሳት፣ ለበሽ ና ሞት የሚዳረጉ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ልቅ ግጦሽ የመኖ ብክነትን የሚያስከትል፣ በሽ ን ለማስፋፋት አመቺ ሁኔ ን የሚፈጥር፣ የመኖ ዝርያ ንዲመናመንና ንዲጠፋ የሚያደርግ፣ የተፈጥሮ ሀብት ና ብዝሐ ሕይወት ጥበቃን የሚያደናቅፍና ፈርጀ ብዙ ችግሮችን የሚያስከትል መሆኑም መዘንጋት የለበትም፡፡

## ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረም የማስወገድ ና የማልማት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ

70. የተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ የሚዘጋጁ የግጦሽ መሬቶች በአላስፈላጊ አረሞች ንዳይወረሩ መቆጣጠር ና ማልማት ይገባል፡፡ በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ የሚገኙትን በቁጥቋጦዎች የተሸፈኑትን ና ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሬቶችን አመቺነት በማጥናት ለግጦሽ የሚውሉበት መንገድ ሊመቻች ይገባል፡፡

71. ይሁን ንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ንደተቻለው የግጦሽ መሬቶችን ከአረም የመከላከል ተግባራት የማይከናወኑ መሆኑን ነው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ/1999-2003/ ውስጥ በአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢ ያለውን በአገር ውስጥ ና መጤ አረሞች /ቁጥቋጦዎች/ የተሸፈኑትን የግጦሽ መሬቶች ተመንጥሮ ለግጦሽ ንዲውል ያካተተ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት የተከለሱ መረጃዎችና የኦዲት ቡድኑ በአካል በተመለከ ቸው ኦሮሚያና አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አላስፈላጊ የሆኑ ቁጥቋጦዎችና አረሞች በግጦሽ መሬት ላይ በስፋት ይተዋል፡፡ ከዚህም ለመረዳት የተቻለው አላስፈላጊ የሆኑ ቁጥቋጦዎችንና አረሞችን ከግጦሽ መሬት ላይ የማስወገድ ተግባር በስፋት አለማከናወኑን ነው፡፡



ፎቶ 6፡ በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳ በግጦሽ መሬት ላይ የሚ የውን አላስፈላጊ አረሞች የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 7፡ በኦሮሚያ ዝዋይ አካባቢ በግጦሽ መሬት ላይ የሚ  የውን አላስፈላጊ አረሞች የሚያሳይ ፎቶ

72. የግጦሽ መሬትን ከአረም የመከላከል፣ በቁጥቋጦ የተሸፈኑ መሬቶችንም ለግጦሽ መሬት የማዋል  ና የማልማት ሥራ ያልተከናወነበትን ምክንያት አስመልክቶ በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር የ ንስሳት ሀብት ከፍተኛ ባለሞያ በሰጡት መልስ ክልሎች በራስ ተነሳሽነት ማከናወን የሚገባቸውን ተግባር ተፈፃሚ ባለማድረጋቸው የተከሰተ ችግር  ንደሆነ ገልፀዋል፡፡

73. የዳልጋ ከብት መኖ  ጥረትን ለመቀነስ ከሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ የግጦሽ መሬቱ መያዝ በሚችለው የከብት ብዛት መጠን/carrying capacity/ መጠቀም ሲሆን  ስካሁን ካለው ሁኔ  ለመረዳት የተቻለው ይህን ተግባራዊ ያለማድረግ ነው፡፡ ይህ ሁኔ  በስፋት ተግባራዊ አለመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሻሻለ የግጦሽ መሬትን በ40 በመቶ ለማሳደግ የያዘው ዕቅድ ግቡን  ንዳይመ  በማድረግ በመኖ  ጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የዳልጋ ከብት ምር ማነት መቀነስን ለመግ ት የሚደረገውን ጥረት ውጤ  ማ  ንዳይሆን አድርጎ  ል፡፡

74. በ ያንዳንዱ አካባቢ ከሚገኘው ውስን የግጦሽ መሬት ተገቢውን መኖ በተፈለገው መጠን በዘላቂነት ለማግኘትና ምር መነቱን ለማጨመር ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል አላስፈላጊ አረምን መቆጣጠር፤ ለየአካባቢው ተስማሚና ምርት ሰጪ የሆኑ የመኖ  ዕዋትና ዛፎችን የማልማትና የአፈርና  ርጥበት(moisture) ዕቀባ ሥራዎችን ማከናወን የግድ ይላል፡፡  ነኚህም ተግባራት በቋሚነት በ ቅድ  የተካተቱ ሊከናወኑ ሲገባ ተግባራዊ ሆነው አልተገኙም፡፡ በዚህም ምክንያት በኦዲቱ በተመለከትናቸው

አካባቢዎች የሚገኙ የግጦሽ መሬቶች ሁሉ አላስፈላጊ አረም የሚ ይባቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

75. በየጊዜው በሚ የው የ ንስሳት ርባ መበራከትና የዳልጋ ከብት ቁጥር ማደግ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመኖ ፍላጐት ለማሟላት ንዲያስችል የመኖ አቅርቦቱ ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሊሰጠውና አስቸኳይ የመፍትሄ ርምጃ ሊወሰድበት፤ ለዚህም ተግባራዊነት የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ንዲሁም የክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮዎች በጋራም ሆነ በተናጠል በአስቸኳይ ተግባራዊ ንቅስቃሴ በመጀመር ላፊነ ቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

በግጦሽ መሬቶች ላይ የሚስተዋለው አላስፈላጊ አረም የመኖ አቅርቦትን የሚያስተጓጉልና ለ ንስሳት ሀብት ልማቱ በአጠቃላይ ንቅፋት መሆኑ፤ በተያያዥነትም በማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ልማት ላይ አሉ ዊ ተፅ ኖ ያለው መሆኑ መ ወቅ አለበት፡፡

## <u>በግጦሽ ሥፍራዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት ስለመኖሩ</u>

76. በአርብቶ አደሩ፣ በከፊል አርብቶ አደሩ ና በአርሶ አደሩ ዘንድ ለሚረቡ የዳልጋ ከብቶች የሚውል የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በግጦሽ ሥፍራዎች መኖር አለበት፡፡ ለከብቶች መጠጥ የሚውለው ውሃ በገንዳ ሊዘጋጅ፣ የናሙና ምርመራ ሊደረግለትና ብክለት ከሚያስከትሉ ነገሮች ሊጠበቅ ይገባል፡፡

77. ይሁን ንጂ በኦዲቱ በተመለከትናቸው የተለያዩ የኦሮሚያ ና አማራ ክልላዊ መስተዳድሮች በኦሮሚያ ቦረና ዞን ያቤሎ ወረዳ ሐሮበኬ ቀበሌ ና ከቡሌ ሆራ ወረዳ ቆማ ሐራ ቀበሌ በስተቀር በሌሎች የተመለከትናቸው ዞንና ወረዳዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት አለመኖሩን ነው፡፡

78. በቦረና ዞን ሐሮ በኬ ቀበሌ የተመለከትነው የውሃ ማከማቻ ኩሬ/pond/ አገልግሎት የሰጠ መሆኑ በጥሩ ጐኑ የሚጠቀስ ተግባር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ነገር ግን ኩሬው በ1967 ዓ.ም የተሰራ ና የጐርፍ ውሃ ማጠራቀሚያ ሲሆን የንፅሕና ይዘቱን ለመከ ተል የሚያስችል የናሙና ምርመራ የሚደረግበት ሥርዐት ያልተዘረጋለት፣ የደለል መከላከያ የሌለው ና ከሰዎች የንፅሕና አገልግሎት /ገላ መ ጠብ/ የሚከለክል አሠራር አለመኖሩን፤ ለ ንስሳቱም የመጠጥ አገልግሎት አመቺነት ንዲኖረው ገንዳ አለመዘጋጀቱን፤ በቦ ው በመገኘት በመመልከት ና ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው የሥራ ላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሁኔ ው በደለል ምክንያት የኩሬውን የመያዝ አቅም የሚቀንስ፤ ከብቶቹም ውሃ

ለመጠጣት ንዲቸገሩ የሚያደርግ፤ ንፅሕናው ንዲጓደልና የበሽ አምጪ ተህዋስያን መራቢያ ንዲሆን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ሆኖ ተገኝቷል።



ፎቶ 8፡ በቦረና ዞን ሐሮ በኬ ቀበሌ ለከብቶች መጠጥ ውሃ የተዘጋጀው ኩሬ ንፅሕናውን ለመጠበቅ የሚያስችል የደለል መከላከያም ሆነ ገንዳ አለመዘጋጀቱን የሚያሳይ ፎቶ።



ፎቶ 9፡ በሐሮ በኬ አካባቢ የኩሬ ውሃ በጭቃ ተሞልቶ የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 10፡ በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳ ሞቶቆማ ሐራ ቀበሌ በተገነባ የከብቶች የመጠጥ ውሃ ግድብ የንፅሕና ክትትል ባለመደረጉ አላስፈላጊ አረሞች በቅለውበት የሚያሳይ ፎቶ፡፡

79. በመሥክ ጉብኝት በተመለከትናቸው የከብቶች መሰማሪያ የግጦሽ ሥፍራዎች ዳልጋ ከብቶች የሚጠጡት ከወራጅ ወንዞች ውሃ ሲሆን ወንዞቹም ሰዎች ለልብስ ና ገላ መ ጠቢያነት የሚገለገሉባቸው ንዲሁም ለተሽከርካሪዎች የ ጥበት አገልግሎት የሚውሉ ከመሆኑም ባሻገር ጥበቱን ሁሉ ውሃ በመቅዳት ከወንዞች ውጭ ማድረግ ሲገባ የሚከናወነው ወንዞቹ ውስጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡



ፎቶ 11፡ በቦረና ዞን አባያ ወረዳ ጉዋንጓ ከተማ አጠገብ ለከብቶች መጠጥነት የሚውለውን የወንዝ ውሃ የመኪና ጥበት በውስጡ ሲከናወንበት የሚያሳይ ፎቶ፡፡



*ፎቶ 12፡ በኦሮሚያ አርሲ ነገሌ ወረዳ ለከብቶች መጠጥነት የሚውለውን የቡልቡላ ወንዝ ውሃ ሰዎች በውስጡ የልብስ ጥበት ሲያከናውኑበት የሚያሳይ ፎቶ፡፡*




*ፎቶ 13፡ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ጫንጮ አካባቢ ለከብቶች መጠጥነት የሚውል የወንዝ ውሃ በውስጡ መኪና ሲ ጠብበት የሚያሳይ ፎቶ፡፡*

**80.** ከላይ በፎቶዎቹ የተመለከቱት አካባቢዎች ከፍተኛ የዳልጋ ከብት ቁጥር አለባቸው ከሚባሉት አካባቢዎች መካከል ሲሆኑ በአንድ ቦ ለግጦሽ የሚሰማሩት ከብቶች ቁጥርም በርካ ነው፡፡ ነኚህ አይነት ቦ ዎችን በመለየትና ትኩረት በመስጠት

ለከብቶቹ የሚያገለግል የንፁህ መጠጥ ውሐ አቅርቦት በገንዳም ሆነ በኩሬ በማድረግ ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ ሳለ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

**81.** ከብቶቹ ከሚጠጡባቸው የወንዞች ውሃም ስለ ንፅሕና ይዘቱ የናሙና ምርመራም የማይደረግ፣ በተፋሰስ ሥፍራዎችና በወንዞች ዳርቻ አካባቢዎች የአፈር መሸርሸርና ደለልን ለመከላከል የሚያስችል የልማት ሥራ የማይከናወን እንዲሁም በወንዞቹ ውስጥ በመሆን የሚደረገውን እንቅስቃሴ የመከ ተልና ብክለት እንዳያስከትሉ የመቆጣጠር ሥራዎችም የሚከናወኑበት ሥርዐት አለመኖሩን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን ከላይ የተመለከቱት ፎቶዎችም ሁኔ ውን የሚገልፁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ወንዞች በሌሉባቸው ቆላማ አካባቢዎች የውሃ አቅርቦት ባለመኖሩ ከብት አርቢዎች እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ርቀት ከብቶችን የነዱ እንደሚጓዙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

**82.** በኦሮሚያ ና አማራ ክልሎች ደጋማ አካባቢዎች የወንዝ ውሃ ለከብቶች የመጠጥ አገልግሎት እንደሚውል፤ ነገር ግን የንፅሕና ይዘቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት አለመኖሩን በአንዳንድ አካባቢዎችም ወንዞች ባለመኖራቸው ምክንያት ውሃ ለማግኘት ረጅም ርቀት የሚጓዙ መሆኑን ከየሥራ ላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ሲራሮ፤ ሻላ፤ አርሲ ነገሌና ሻሸመኔ አካባቢዎች በ2000 ና 2001 ዓ.ም በውሃ ጥረት ምክንያት ብዙ ከብቶች እንደሞቱ የምዕራብ አርሲ ዞን የ ንስሳት ሀብት ጤናና ገበያ ጽ/ቤት ተወካይ ጋር ከተደረገ ቃለምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በአማራ ክልልም በተለይ ወንበርማ ወረዳ ደብረኤልያስና በለሳ አካባቢዎች በውሃ ጥረት እንደሚጠቁና በክልሉ የከብት ሀብት ልማት ላይ ያለው ዋነኛ ችግር የውሃ አቅርቦት ማነስ መሆኑን የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የግብርና ቴክኖሎጂ ብዜትና የግል ባለሀብት ድጋፍ ባለሙያ ገልፀዋል፡፡

**83.** በደብዳቤ ልውውጥ በተሰበሰበ መረጃም በትግራይ፤ ሐረሪ ና ጋምቤላ ክልሎች የወንዝ ና ኩሬ ውሃ ለከብቶች የመጠጥ አገልግሎት እንደሚውል፤ ነገር ግን ጥረት መኖሩን፤ በደቡብ ክልል በተለይ በአርብቶአደሩ ዘንድ /ቆላማ አካባቢዎች/ ከፍተኛ የውሃ ችግር መኖሩን፤ በድሬዳዋ ና አፋር ክልሎች የወንዝም ሆነ የኩሬ ውሃ አለመኖሩንና የውሃ አቅርቦት ጉዳይ ዋነኛው ችግር እንደሆነ በደብዳቤ ገልፀዋል፡፡

**84.** ስለሁኔ ው የግብርና ሚኒስቴር የ ንስሳት ሀብት ልማት ከፍተኛ ባለሞያ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ይህ የባለድርሻ አካላትን የሚመለከት መሆኑንና ችግሩ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ብቻ ሳይሆን የሌሎችም በተለይም የአርብቶ አደር ክልሎች ላይ የጐላ መሆኑ፤ የአቅም ውሱንነት /የበጀት አለመኖር/ ና ቅንጅ ዊ አሰራር ችግር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

85. ይሁንና ኛ ንደተረዳነው እና በውሃ ሀብት ፖሊሲውም እንደተገለፀው ለእንስሳት የመጠጥ ውሃ ማቅረብ መሰረ ዊ ጉዳይ ሆኖ ሳለ ይህ አለመሟላቱ ለ ንስሳት ሀብት ዘርፉ ተገቢው ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በኩሬ መልክ ለተዘጋጀው ውሃ የደለል መከላከያና የንፅሕና ክትትል አለመደረጉ፤ ለከብቶች የመጠጫ ገንዳ አለመዘጋጀቱ ና የወንዞች ብክለትን ለመከላከል የሚያስችል ተግባር አለመከናወኑ አግባብነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

86. ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የዳልጋ ከብቶች ጤንነቱ ያልተረጋገጠና ንፁህ ያልሆነ ውሃ መጠጣ ቸው ለተለያዩ በሽ ዎች ንዲጋለጡና ጤንነ ቸው ንዲ ወክ፤ ምር ማነቱን የሚቀንስ፤ ብሎም ለሞት የሚዳርግ በመሆኑ የ ንስሳት ሀብት ልማቱን የሚያደናቅፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የሚመለከ ቸው የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሥርዓት በመዘርጋት አፋጣኝ ርምጃ ንዲወሰዱ ናሳስባለን፡፡

## የዳልጋ ከብት ጤና አገልግሎት ስለመዳረሱ ና አጥጋቢ ስለመሆኑ

87. የዳልጋ ከብቶችን ከበሽ ለመከላከልና በጤና ጉድለት ምክንያት የሚከሰተውን ሞት ለመግ ት የሚያስችል የጤና አገልግሎት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ሥርዓቱም የክትባትና ሕክምና አገልግሎት፣ የመድሐኒት አቅርቦት፣ ክሊኒኮችና የመገልገያ መሳሪያዎች፣ የበሽ ክትትልና ቁጥጥር ተግባራት፣ የጤና ሞያተኞች አቅርቦት በየአካባቢው ላለው የዳልጋ ከብቶች ጤና አገልግሎት ፍላጐት ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

88. በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ ና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች በየወረዳው በመዘዋወር ከተከናወኑ የመስክ ሥራዎችና ከሌሎቹ ክልል መስተዳድሮች ጋር በደብዳቤ መላላክ በተደረገ ግንኙነት የ ንስሳት ጤና አገልግሎት በየአካባቢው ላለው ፍላጐት ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በሚያስችሉ ደረጃ ላይ አለመሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89. የክትባት አገልግሎት አለመዳረስና ወቅቱን ጠብቆ በቋሚነት በ ቅድ ተይዞ የሚከናወን ባለመሆኑ ለ ንስሳት ሞት አንዱ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን አባያ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች /ዲቢቻና ጐሎልቻ/ ብቻ በ2002 ዓ.ም ከግንቦት መጀመሪያ ስከ ሐምሌ አጋማሽ ባለው የ2 ወር ተኩል ጊዜ ወስጥ ብዛ ቸው 4562 የሆኑ የዳልጋ ከብቶች መሞ ቸውን ከወረዳው የ ንስሳት ሀብት ልማት ጤናና ገበያ ጽ/ቤት ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የኦዲት ቡድኑ በነሐሴ 13 ቀን 2002 ዓ.ም በተጠቀሱት ቀበሌዎች በአካል በመገኘት ከአካባቢው ነዋሪዎችና የገበሬ ማህበር ሊቃነ መናብርት ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ የሞቱት ከብቶች ቁጥር 7000 ንደሚሆን፤ የሞት ቁጥሩ ይለያይ ንጂ

በየዓመቱ የዚህ አይነት ችግር ንዳለ፤ በክትባት አገልግሎት አለመኖርና በመድሐኒት ጥረት ምክንያት አርብቶአደሩ ሕገወጥ መድሐኒቶችን ለመጠቀም መገደዱን ገልፀዋል::



ፎቶ 14: በዲፒቻ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ከቀበሌው ሊቀመንበር ና ከወረዳው ቢሮ ተወካይ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ና የመስክ ጉብኝት የሚያሳይ ፎቶ::

**90.** በሽ ዎቹም በአንደኛ ደረጃ አባሰንጋ፣ አባጎባ፣ የሳንባ ትል(CBPP)፤ በሁለተኛ ደረጃ (Bovine pasteurellosis) ና በሶስተኛ ደረጃነት የአፍተግር(Foot and Mouth disease) ና የቆዳ መጉረብረብ/ ከክ/ መሆናቸውን ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎችና ለክልሎች በደብዳቤ በተላከ መረጃ መሰረት ለማወቅ ተችሏል::

**91.** የሕክምና አገልግሎትንም በተመለከተ በተለይ የ ንስሳት ሀኪም (Veterinary Doctor) ለሚያስፈልጋቸው ክሊኒኮች አለመሟላቱን ለማወቅ ተችሏል:: በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን/ሻሸመኔ/ ለዞኑ የሚያስፈልገው የ ንስሳት ሐኪም ብዛት 12 ሲሆን ያሉት ግን 6 ብቻ መሆናቸውን የዞኑ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ኤክስቴንሽን ሞያተኛ ገልፀዋል::

**92.** በአማራ ብሔራዊ ክልል በአጠቃላይ በክልሉ ያሉት የ ንስሳት ሀኪሞች ብዛት 81 ያህል ሲሆን ነኚህም ከሚፈለገው ቁጥር ግማሽ ያህል ብቻ መሆኑን በክልሉ ግብርና ጽ/ቤት የግብርና ቴክኖሎጂ ብዜትና የግል ባለሀብት ድጋፍ ባለሙያ ገልፀዋል:: በዚሁ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረብርሐን ከተማና አካባቢው /ባሶና ወራና ወረዳ/ በክልሉ ከፍተኛው የ ንስሳት ርባ የሚከናወንበት ሆኖ ሳለ፤ አንድም ሀኪም አለመኖሩ ተገልጿል:: በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን በአጠቃላይ በዞኑ የሚገኙ የ ንስሳት ሀኪሞች ብዛት 7 ሲሆን ከሚፈለገው ከግማሽ በ ች መሆኑን የዞኑ ጽ/ቤት ተወካይ

ገልፀዋል፡፡ አንድ የ ንስሳት ሀኪም ለምን ያህል ከብቶች መድረስ ንዳለበት በአገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በየክልሎቹ የወጣ መሥፈርት አለመኖሩንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 2፡ በየክልሉ የጤና ሞያተኞች ብዛትና አንድ የከብት ሐኪም ለምን ያህል ከብት አገልግሎት ንደሚሰጥ የሚያሳይ**

| የክልሉ ስም | የከብት ብዛት | የ ንስሳት ሐኪም ብዛት | ረዳት የ ንስሳት ሐኪም ብዛት | የከብት ጤና ቴክኒሽያን | 1 ሐኪም ለምን ያህል ከብቶች ንደሚሆን የሚያሳይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር | 70,941 | 5 | 16 | 1 | 1:14,188 |
| አማራ ክልል | 12,748,995 | 81 | - | - | 1:157,395 |
| ጋምቤላ ክልል | መረጃ የለም | 4 | 122 | - | መረጃ የለም |
| ኦሮሚያ ክልል | 22,457,335 | 147 | 1,611 | 105 | 1:152,743 |
| አፋር ክልል | 2,336,539 | 19 | 72 | 240 | 1:122,976 |
| ትግራይ ክልል | 3,504,829 | 17 | 186 | 40 | 1:204,166 |
| ደቡብ ክልል | 9,731,402 | 127 | 1,076 | 84 | 1:76,625 |
| ሐረሪ ክልል | 44,199 | 2 | 7 | 2 | 1:22,099 |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል | መረጃ የለም | - | - | - | መረጃ የለም |
| ሶማሌ ክልል | መረጃ የለም | - | - | - | መረጃ የለም |

93. የመድሐኒት አቅርቦትን በተመለከተ በወረዳም ሆነ በክልል ደረጃ ጥረት መኖሩን በመስክ ሥራ ባደረግነው ጉብኝትና ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይኸውም በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን አባያ፣ ቡሌሆራ ና ያቤሎ ወረዳዎች ከፍተኛ የሆነ የመድሐኒት አቅርቦት ጥረት መኖሩን ከየወረዳዎቹ ግብርና ጽ/ቤት ተወካዮችና በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱት መንግስ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/ወርልድ ሎተራን ፌዴሬሽን ና ወርልድ ቪዥን/ አስተባባሪዎች ጋር ከተደረገ ቃለምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ክልል ምዕራብ አርሲ ዞን ከ ንስሳት ጤና ጋር በተያያዘ ዋናው ችግር የመድሐኒት አቅርቦት ጥረት ንደሆነ የዞኑ ግብርና ቢሮ ተወካይ አስረድተዋል፡፡ በሰሜን ሸዋ ዞን/ፍቼ/ በተመሳሳይ የመድሐኒት አቅርቦት ማነስ ትልቁ የአካባቢው ፈ ኝ ጉዳይ ንደሆነ የዞኑ ጽ/ቤት ተወካይ ገልፀዋል፡፡

94. በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ባሶና ወራና ወረዳ /ደብረ ብርሀን/ በክልሉ ከፍተኛው የ ንስሳት ርቢ የሚከናወንበት ወረዳ ንደሆነና የመድሐኒት ጥረት በአንደኛ ደረጃ የሚጠቀስ ችግር መሆኑን የወረዳው ጽ/ቤት ላፊ ና የግብርና ኤክስቴሽን የሥራ ሂደት ፈፃሚ በጋራ በሰጡት ቃለምልልስ ገልፀዋል፡፡ የመድሐኒት አቅርቦት ማነስ በአጠቃላይ የክልሉ ችግር መሆኑንም የክልሉ ግብርና ቢሮ የግብርና ቴክኖሎጂ ብዜትና የግል ባለሀብት ድጋፍ ባለሙያ ገልፀዋል፡፡

95. በትግራይ ክልልም በበጀት ማነስ ምክንያት የ ንስሳት ጤና አገልግሎቱ ውጤ ማ ንዳልሆነ የክልሉ ግብርና ቢሮ የምርምር ኤክስቴንሽን የሥራ ሂደት ባለቤት በደብዳቤ ገልፀዋል፡፡ የክሊኒኮችና የመገልገያ መሣሪያዎች አለመሟላትም የጤና አገልግሎት ዘርፉ የሥራ ማነቆ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ና በሐረሪ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የ ንስሳት ክሊኒኮችና ጤና ኬላዎች በቁጥርም ሆነ በመገልገያ መሣሪያዎች አቅርቦት ያልተሟሉ መሆኑን የክልል ጽ/ቤቶቹ በደብዳቤ ለቀረበላቸው መጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡

96. በአካል በመገኘት የኦዲት ቡድኑ ከተመለከ ቸው መካከልም በአማራ ክልል ባህርዳር ከተማ የሚገኘው የወረዳው የ ንስሳት ሕክምና ክሊኒክ የ ማሚ ከብቶች ማሣደሪያ/ማቆያ/ በረት ፈራርሶ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤ ለጤና ሞያተኞቹ ግልጋሎት ይሰጥ የነበረው የ ጅ መ ጠቢያና የላቦራቶሪ አገልግሎት መሥጫ በመበላሸቱ ውሀ የማያገኙ መሆኑ፤ ክሊኒኩ የሚገኘው ከፍተኛ የተሽከርካሪ ንቅስቃሴ ባለበት አቧራማ መንገድ ዳርቻ ሲሆን ወደ ክሊኒኩ፤ ላቦራቶሪውና ግምጃ ቤቱ የሚገባው አቧራ ሥራን የሚያውክ ከመሆኑም ባሻገር የፅዳት ሠራተኛ ሳይመደብ ሁለት ዓመ ት ንዳለፉት፤ ይኸው ክሊኒክ ከከተማው በግምት የ4 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለክሊኒኩ የጤና ሞያተኞች /ሐኪሙን ጨምሮ/ የትራንስፖርት አገልግሎትም ሆነ የሞተር ሳይክል አለመኖሩ በአጠቃላይ የክሊኒኩ ሥራ ላይ ንቅፋት ንደሆነባቸው የክሊኒኩ ላፊና ሐኪም አስረድተዋል፡፡

97. በኦሮሚያ ክልልም በቦረና ዞን አባያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው ክሊኒክ የሚጠቀምበት የከብቶች ማቆሚያ(cattle crush) ከ ንጨት የተሰራ፤ ወለሉም አፈርና ጉድጓድ የሆነ፤ መጠለያ የሌለው ሲሆን ተገነጣጥሎና ወለሉ በጭቃ በመሞላቱ መገልገል አለመቻላቸውን በአካል ለመመልከትና ከወረዳው ጽ/ቤት ላፊ ጋር በተደረገ ቃለምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላም በኩል በዚሁ ወረዳ ጉሎልቻ ቀበሌ የሚገኘው ክሊኒክ ደረጃውን የጠበቀ የከብቶች ማቆሚያ የተሰራለት ቢሆንም ክሊኒኩ አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ የከብቶች ማቆሚያው(cattle crush) በአያያዝ ጉድለት ምክንያት የአረም መብቀያ ሆኖ ተገኝቷል፡፡



***ፎቶ 15፡ አባያ ወረዳ፤ ጎሎልቻ ቀበሌ አገልግሎት ለመሥጠት የማይመች የከብቶች ማከሚያ በ*** (cattle crush)



***ፎቶ 16፡ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ፍቼ ከተማ የሚገኝ የ ንስሳት ክሊኒክ የሚገለገልበት የከብቶች ማከሚያ በረት***(cattle crush) ***የተሰባበረ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ***

**98. በባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ሮቢት ባ ቀበሌ የሚገኝ ሞዴል ገበሬም ከኦዲተሮች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ሐኪሞች ጐብኝተውን ስለማያውቁና ነሱ የሚገኙበት በ ከብት ይዞ ለመሄድ ከርቀቱ አንፃር የማይቻል በመሆኑ ከብቶቻቸው**

በበሽ ስለሚያልቁባቸው በከብት ርባ ላይ ለመሰማራት የነበራቸውን ተነሳሽነት ንዳስተጓጐለው ገልፀዋል፡፡ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ባሶና ወራና ወረዳ/ደብረ ብርሀን/ የ ንስሳት ሐኪም በወረዳው ንደሌለ የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ላፊ አስረድተዋል፡፡

99. በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳ በዳልጋ ከብት ብዛት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ከሚገኙት መካከል መሆኑንና በወረዳው አንድም የ ንስሳት ሐኪም አለመኖሩን የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ተወካይ ገልፀዋል፡፡ በዚሁ ዞን የሚገኙት የአባያ ና ያቤሎ ወረዳዎችም ሐኪም የሌላቸው መሆኑን የየወረዳው ጽ/ቤት ተወካዮች ገልፀዋል፡፡

100. ክሊኒኮች ከአገልግሎት ፈላጊው ሕብረተሰብ ርቀው የሚገኙ በመሆኑም የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ንዳልቻሉ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በአባያ ወረዳ የሚገኙ ቀበሌ ነዋሪዎችና ከወረዳው የግብርና ጽ/ቤት ላፊ ጋር በተደረገ ውይይት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ጉሎልቻ ቀበሌ ወደሚገኘው ክሊኒክ ለመድረስ የፈጫ ቀበሌ ነዋሪዎች 18 ኪ.ሜ መጓዝ ንዳለባቸውና ሌሎች ሁለት አጐራባች ቀበሌዎችም ከ40 ስከ 60 ኪ.ሜ ያህል ንደሚጓዙ ተገልጾልናል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን ሁኔ ዎች አስመልክቶ ጉዳዩ ለሚመለከ ቸው የሥራ ላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ከዚህ በ ች የተመለከተውን መልስ ሰጥተዋል፡፡

101. በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር የ ንስሳትና ፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክተር በሰጡት መልስ በሽ ዎችን መከላከል ላይ ያለው ችግር አስገዳጅ የክትባት ስርዓት(mandatory vaccination) አለመኖሩ ንደሆነ፣ በፌዴራል በኩል የሚደረገው የክትባት አገልግሎት በሽ ው ፋ የማይሰጥ ና ድንበር ዘለል ለሆኑ በሽ ዎች ብቻ ንደሆነ ሲገልፁ በዚሁ ዳይሬክቶሬት የድንበር ዘለል በሽ ዎች ቁጥጥር ከፍተኛ ሞያተኛ በሰጡትም ማብራሪያ በየክልሉ ያለውን ችግር ለማቃለል ክሊኒኮች የተገነቡ ቢሆንም በሰው ሐይል፣ መድሐኒትና መገልገያ መሣሪያዎች አለመሟላት ምክንያት ለአገልግሎት ባለመዋላቸው መገልገል ንዳልተቻለ፣ ለዚህም ምክንያት ሊሆን የሚችለው የበጀት ጥረት ንደሆነ፣ ክሊኒኮች ሲገነቡም የአገልግሎት ፈላጊዎቹንና አመቺነት /አስፈላጊ ቦ / ያገናዘበ አለመሆኑ ንደሚስተዋል፣ የ ንስሳት በሽ ዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አዋጅ በ1994 ዓ.ም የወጣ ቢሆንም የማስፈፀሚያ ደንብ ዝግጅቱ በሂደት ላይ በመሆኑ ተፈፃሚነት አለማግኘቱ ለችግሮቹ መከሰት ምክንያት ንደሆኑ አብራርተዋል፡፡

102. ለኦሮሚያ ክልል ለ ንስሳት ሐብት ልማት ጤና ጥበቃና ገበያ ኤጀንሲ ተወካይ ና ከፍተኛ የዘርፉ ሞያተኞች ለቀረበላቸው ቃለ ምልልስ በጋራ በሰጡት መልስ ውጤ ማ ላልሆኑት አካባቢዎች በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው የአስተዳደር ብቃት ማነስ ንደሆነ፣ የክሊኒኮች ሥርጭትም በጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆን፣

በፖሊሲ ደረጃ ከግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ጋር የተጠናከረ የሥራ ግንኙነት አለመኖር የሚጠቀሱ ጉዳዮች ንደሆኑ አብራርተዋል፡፡

**103.** ኛ ንደተረዳነው ለ ንስሳት ጤና አገልግሎቱ በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ በክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮዎች/ኤጀንሲዎች/ የተሰጠው ትኩረት በቂ አለመሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ከላይ በጥቂቱ የተገለፁት ጉዳዮች አስረጂ ከመሆናቸውም ባሻገር የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል በተከ ይ ባደረጓቸው የአራተኛው፣ አምስተኛውና ስድስተኛው ዓመ ዊ ስብሰባዎች /ከ1999-2002/ ላይ ስለጤና አገልግሎት የተነሳ ርዕስም አለመኖሩ ነው፡፡

**104.** የዳልጋ ከብቶች በአቅራቢያቸው ተገቢውንና ፈጣን የጤና ና ክትባት አገልግሎት ስካላገኙ በበሽ ና ሞት ምክንያት ለሐገር ልማት ያለውን አስተዋፅኦ ንደሚያስተጓጉል ግንዛቤ ሊወሰድበት፣ አገሪቷ ከምት ወቅበት የ ንስሳት ሀብትም በሚጠበቀው ደረጃ ተጠቃሚ ለመሆን አለመቻልም ምክንያት መሆኑን ለማስገንዘብ ንወዳለን፡፡

## <u>የአገር ውስጥ የዳልጋ ከብት ዝርያ የማሻሻያ ተግባርን በተመለከተ</u>

**105.** በሀገር ውስጥ በሥጋና በወተት ምር ቸው የተሻለ ሕብለ-በራሄ (Genetic potential) ያላቸው የዳልጋ ከብቶች ዝርያቸው ተጠንቶ ጥቅም ላይ ንዲውሉ መደረግ ይኖርበ ል፡፡ ስለውጤ ማነ ቸውም ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

**106.** በሀገር ውስጥ በስጋ ምር ቸው የተሻለ ምርት በሚሰጡት ላይ ጥናት ተደርጎ በደረጃ የቦረና የፎገራ የከረዩ የመሳሰሉት ጥሩ ምርት መስጠት ንደሚችሉ ቢ ወቅም፤ በሥጋ ምርት ዙሪያ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ግን አለመጀመሩ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም የተሻለ ሥጋ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ የሀገር በቀል ዳልጋ ከብቶች ንዳይባዙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በሥጋ ምርት ዙሪያ የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ያልተጀመረበትን ምክንያት በግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ባለሙያ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የስጋ ማሻሻያ ምርምር ጣቢያ አለመኖር፣ ለሥጋ ሀብት ልማት ቅድሚያ ያለመስጠት፣ የውጭ ገበያ ፍላጎት የቁም ንስሳት ላይ በመሆኑ ለዳልጋ ከብት ስጋ ትኩረት አለመስጠት፣ የርቢ ፓሊሲና ደንብ የሌለ በመሆኑና የስጋ ዝርያን ለማሻሻል ተብሎ ከውጭ የተሻለ ዝርያ ማስገባት አለመቻል ምክንያት ንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

**107.** የወተት ምርትን በተመለከተ ከዳልጋ ከብት ከሚገኘው አጠቃላይ የወተት ምርት ውስጥ 97% በላይ የሚገኘው ከሀገር ዝርያ ከብቶች ሲሆን፣ ከተሻሻሉ ዝርያዎች የሚገኘው የወተት መጠን 3% የማይበልጥ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው የዝርያ ማሻሻያ ተግባር ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑን ነው፡፡

የወተት ምርትን ለማሻሻል የተከናወነ ያለ ንቅስቃሴ ቢኖርም አሁንም የሀገሪቱ የነፍስ ወከፍ የወተት ፍጆ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ወተትን ከውጭ በማስመጣት ሀገሪቱ ለከፍተኛ ወጭ የተዳረገች መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

108. ለዚህም በግብርና ሚኒስቴር የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ባለሙያና የግብርና ምርምር ኢንስቲቱዩት ንስሳት ምርምር የሥራ ሂደት ዳይሬክቶሬት ስለዚህ ጉዳይ ተጠይቀው፤ በሰጡት ምላሽ የተሻሻሉ ጊደሮች ስርጭትን በተመለከተ በመንግስት ስር የነበሩ የምርምር ጣቢያዎች ወደ ግል ባለሀብት ሲዛወሩ መከተል የሚገባቸውን ሥርዓት፣ ደንቦችና ግዴ ዎችን ያስቀመጠ አለመሆኑ፤ የምርምር ጣቢያው ለ ቀደለት ዓላማ መዋሉን ለመከ ተልና ለመቆጣጠር ሁኔ ዎች ያልተመቻቹ መሆኑ፤ የማባዣ ማዕከሎች ውሱን መሆን፤ ወደ ግል ሲዘዋወሩ የዋጋ ውድነት ስለሚኖረው ተጠቃሚው የማያገኝ መሆኑና የመሳሰሉት ምክንያት ንደሆኑ ገልጸዋል።

109. ነገር ግን ይህን ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው መደበኛ የልማት አካላት ግንኙነት ስብሰባ ላይ በማንሳት የግል ባለ ብቱን በማሳተፍ ጭምር ከክልሎች ጋር በቅንጅት ለመፍ ት የተደረገ ሙከራ አለመኖሩ ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አለመሰጠቱን ያሳያል።

## ለሞያተኞችና ለአርብቶ አደሮች የሚሰጥ የግንዛቤ ማዳበሪያና ሥልጠና ስለመኖሩ

110. የ ንስሳት ሀብት ልማትን ለማጠናከርና በ ያንዳንዱ ደረጃ ሊኖር የሚችለውን ጥቅም ለማረጋገጥ ንዲያስችል በልማት ሥራው ላይ የተሰማሩ ሞያተኞች፤ አርብቶአደሮች፤ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች ለልማቱ ገዛ የሚያደርግ የግንዛቤ ማዳበሪያ ና ሥልጠና የሚያገኙበት ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል። ለዚሁም ንዲረዳ የግንዛቤና ክህሎት ክፍተቶች የተለዩ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ባለው መልኩ መስጠት ንዲችሉ በ ቅድ የተያዙ፤ተፈፃሚ ለመሆናቸውና ለውጥ ያመጡ መሆኑም ክትትል የሚደረግበት አሰራር መኖር አለበት።

111. ከኦዲት ውጤቱ ለመገንዘብ ንደተቻለው በየክልሉ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ለአርብቶ አደሮች፤ ከፊል አርብቶ አደሮች ና አርሶ አደሮች፤ በተወሰነ ደረጃም ለሞያተኞች የሚሰጥ ሥልጠና መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል። ይሁን ንጂ የሚሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫ ና ሥልጠናዎች በቅድሚያ የመነሻ ጥናት /የሥልጠናዎቹን አስፈላጊነት፤ በምን አይነት ጉዳይ ላይ ክፍተት ንዳለ፤ ቅድሚያ የሚሰጠውን የመለየት፤ ለነማንና ለምን ያህል ሰልጣኞች፤ ሥልጠናውን ማን ይስጥ፤ ወዘተ/ የማይከናወን፤ የተሰጡት የግንዛቤ ማስጨበጫዎችና

ሥልጠናዎች ለውጥ ማምጣ ቸው ክትትል የማይደረግበት፤ ሥልጠናውም ወጥነት ያለው ሳይሆን ሥልጠናውን በሚሰጠው አካል የሚወሰን መሆኑ ውቋል::

112. ለአርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና ገበሬዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች ከ1999-2001 ዓ.ም ባለው የ3 ዓመ ት ጊዜ፣ ለምን ያህል ሰዎች በምን አይነት ጉዳይ ላይ ሥልጠና ንደተሰጠ ለማወቅ ከተሰበሰበ መረጃ ለመገንዘብ ንደተቻለው በትግራይ ክልል ምንም የግንዛቤ ማስጨበጫ ንዳልተሰጠ፤ በአፋር ክልል በቁጥር መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለና በቀጥ ም ከዳልጋ ከብት ልማት ጋር የተገናኘም ባይሆን በ ንስሳት በሽ ቁጥጥርና የአዕዋፍ ኢንፍሉዌንዛ ጋር በተያያዘ ሥልጠና ንደተሰጠ፤ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በቁጥር መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ በ ንስሳት ርባ ና መኖ ልማት ላይ ንደተሰጠ፤ በኦሮሚያ ክልልም በቁጥር መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ነገር ግን በየወረዳው ሁለገብ ሥልጠና ንደተሰጠ፤ በአማራ ክልልም በቁጥር መረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ ሁለገብ የግንዛቤ ማዳበሪያ ንደሚሰጥ፤ ሥልጠናውም በየቀበሌው በተሰማሩ የልማት ሰራተኞች አማካኝነት ንደተሰጠ፤ በሐረሪ ሕዝቦች ለ144 ሰዎች፤ በጋምቤላና ድሬዳዋ በያንዳንዳቸው ለ90 ና 28 ከፊል አርብቶ አደሮች በቅደም ተከተሉ ሥልጠና ንደተሰጠ ተገልጿል::

***ሠንጠረዥ 3: ከ1999-2001 ዓ.ም ባለው ጊዜ የተሰጡ ሥልጠናዎች***

| ተ.ቁ | የክልሉ ሥም | ሥልጠና የወሰዱ ሠልጣኞች ብዛት | የሥልጠናው አይነት | ሥልጠናውን የወሰዱ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ድሬዳዋ | 28 | ጤና ቁጥጥር | አርብቶ/ከፊል አርብቶአደር |
| 2 | ጋምቤላ | 90 | ጤና አገልግሎት | “ |
| 3 | አፋር | አይ ወቅም | በሽ ቁጥጥርና አዕዋፍ ኢንፍሎዌንዛ | “ |
| 4 | ትግራይ | የለም | አልተሰጠም | “ |
| 5 | ደቡብ ብሔሮች | አይ ወቅም | ንስሳት ርባ ና መኖ | አርብቶ/ከፊል አርብቶአደርና ለሞያተኞች |
| 6 | ሐረሪ | 123<br>21 | - ርባ ና መኖ ልማት<br>- ጤና | አርሶ አደሮች (ከህብረተሰቡ ለተመረጡ) |
| 7 | ኦሮሚያ | መረጃ የለም | ሁለገብ ሥልጠና | አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች |
| 8 | አማራ | መረጃ የለም | ሁለገብ ግንዛቤ ማዳበሪያ | ለልማት ሠራተኞች፤ ለአርብቶ/ ከፊል አርብቶ አደር (በልማት ሠራተኞች አማካኝነት) |

113. በግብርና ሚኒስቴር አማካኝነት ከ1999-2001 ዓ.ም ባሉት ሶስት አመ ት በቁጥር መረጃ ያልቀረበለት በአፋርና ሶማሌ ክልሎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ንዲሁም የግብርና ቢሮ ተወካዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ንደተሰጠ ተገልጿል:: በኦሮሚያና አማራ ክልሎች ከሚገኙ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች ተወካዮች ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስም ለመገንዘብ ንደተቻለው በየቀበሌው በተመደቡ የልማት ሰራተኞች አማካኝነት አስፈላጊ ነው ብለው ባመኑበት ጉዳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለሕብረተሰቡ ንደሚሰጡ፤ ነገር ግን ለሞያተኞች የተሰጠ ሥልጠና አለመኖሩን ነው::

114. ከላይ ንደተመለከተው ከፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ና ከሁሉም ክልሎች /ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ሱማሌ ክልሎች በስተቀር/ ከተገኘ መረጃ መረዳት ንደሚቻለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናው በ ርባ ፤ መኖ ና ጤና ቁጥጥር ላይ ብቻ ያተኮረ፤ ለምን ያህል ሰልጣኞች ንደተሰጠ በቁጥር ንኳን የማይ ወቅ፤ ሥልጠናውም የሚሰጠው በአብዛኛው በየቀበሌው በሚገኙ የልማት ሠራተኞች አማካኝነት የመሆኑ፤ የሰልጣኞች ብዛትም በ3 ዓመ ት ጊዜ ውስጥ ጥቂት መሆኑ /ለምሳሌ ድሬዳዋ የገጠሩ ሕብረተሰብ በዋናነት ከብት አርቢ ና ቁጥሩም ከፍተኛ ሆኖ ሳለ በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ 28 ብቻ ሥልጠና ማግኘ ቸው/ ከነጭራሹም በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥልጠና ያልተሰጠበት ክልል መኖሩ/ትግራይ ክልል/፤ ከአንድ የሥልጠና አይነት በስተቀር ያልተሰጠበት ክልል መኖሩ /ጋምቤላ ክልል/፤ የተሰጡት ሥልጠናዎች በተግባር ላይ ለመዋላቸውና ለውጥ ያመጡ ለመሆኑ የክትትልና ግምገማ ሪፖርት አለመዘጋጀቱን ነው:: ከዚህ በተጨማሪም የሞያተኞችን ክህሎት ለማጐልበት የሚያስችል የሥልጠና መርሐ ግብር አለመኖሩን ነው:: ሥልጠና የተሰጠባቸው ለሥልጠና የተዘጋጁ ፅሑፎችም ንዲቀርቡልን ተጠይቀው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው ይዘቱንም ለማወቅ አልተቻለም::

115. ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው የሥልጠና መርሐ ግብር በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ በክልል ቢሮዎች አለመኖሩን፣ በዚህም ምክንያት የመነሻ ፍላጐት ጥናት ንዲከናወንና በ ቅድ የተያዘ አለመከናወኑን ነው:: በመስክ ሥራ ጉብኝት በተደረገባቸው ወረዳዎችም በአርብቶ አደሩና በገበሬው ዘንድ ስለ ንስሳት ሐብት ልማት በቂ ግንዛቤ አለመኖሩን፤ ሥልጠናውም ለህብረተሰቡ አለመዳረሱንና ተከ ይነት ባለው መልኩ አለመከናወኑን ነው:: ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በአማራ ክልል ለዳልጋ ከብቶች በበሽ የመያዝና የመሞት ምክንያት ሕብረተሰቡ ከብቶቹን ለማስከተብ ፈቃደኛ አለመሆኑ ይህም በግንዛቤ አለመጐልበት ምክንያት ንደሆነ ከክልሉ ከፍተኛ የ ንስሳት ሀብት ሞያተኛ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ ከመቻሉም በላይ በየትኛውም በአካል ከተመለከትናቸው የኦሮሚያና አማራ ክልል ከሚገኙ አካባቢዎች ስለአካባቢ ና የግል ንፅሕና ንዲሁም የ ንስሳት ንፅሕና

አጠባበቅ ና ደህንነት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ያለው የግንዛቤ ደረጃ አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ የከብቶች በረት አሰራር፣ የግጦሽ መሬትና የመኖ አያያዝ፣ ውሃ አጠባበቅና አቅርቦት ንፅህና የጉደለውና ትኩረት የማይሰጠው መሆኑን ነው፡፡ በሽ የያዘውን ከብት በቀላሉ የመለየትና ወደ ህክምና ጣቢያ የመውሰድ፣ በሽ ከመከሰቱ በፊትም ተገቢውን ህክምናና ክትባት ንዲያገኙ አለማድረግ፣ ከብቶች ለመጠጥ የሚጠቀሙበትን የወንዝ ውሃ ከብክለት መጠበቅ ቀርቶ ለብክለቱ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ሆኖ መገኘቱ የሚጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡



ፎቶ 17፡ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ፅጌ ወረዳ ንፅህና የጎደለውና በመጠኑም ቢሆን ደረጃውን ያልጠበቀ የበረት አሰራር፡፡



ፎቶ 18፡ በኦሮሚያ ቦረና ዞን ያቤሎ አካባቢ(ደሪቶ ቀበሌ) አህያና ዳልጋ ከብቶች አለአግባብ በአንድ ላይ ና ንፅህና በጎደለው በረት ውስጥ መሆናቸውን የሚያሳይ ፎቶ፡፡



ፎቶ 19፡ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ሙከጡሪ አካባቢ ደረጃውን ያልጠበቀና ንፅሕና የጐደለው
የከብቶች በረት / ሰላሌ ወተት ልማት ድርጅት/የግል/

116. ከጤና ሞያተኞቹ ጋር በተደረገ ውይይትም የ ንስሳቱ በበሽ በተደጋጋሚ የመያዝ አንዱ ምክንያትም የአካባቢ ና የግል ንፅሕና ጉድለት መሆኑን ነው፡፡ በየቀበሌው የተመደቡ የ ንስሳት ና የጤና ልማት ሠራተኞች ያሉ ቢሆንም፤ ለናሙና የሚሆኑ ተጨባጭ ሥራዎች ለመሥራ ቸው ማስረጃም ሊቀርብ፤ በአካልም ሊ ይ አልቻለም፡፡ የጓሮ የመኖ ልማት ስለመኖር፣ የ ንስሳት ቁጥርን መጥኖ በማርባት ምር ማ መሆን የሚቻል መሆኑ በአርብቶ አደሩ ዘንድ ተፈፃሚ አለመሆኑ፣ ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረምን አለመከላከል፣ ለከብቶች መጠጥ የሚውል የወንዝ ውሃ ውስጥ ልብስ የማጠብና ገላ የመ ጠብን...ወዘተ የሚስተዋሉትና የተለመዱ ሁኔ ዎች የግንዛቤ ማነስን ያመላክ ሉ፡፡

117. በሞያተኞች ዘንድም የ ንስሳት ሐኪሞች ከትምህርት ቤት መጥተው በቀጥ የህክምናውን ዘርፍ ላፊነት ተረክበው ነፃ/independent/ ሆነው ንደሚሰሩና ልምድ የሚያካፍላቸው ነባር ሞያተኛ በሌለበት ሥራ የሚሰሩ መሆኑንና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናም ሆነ የመግቢያ ገለፃ(orientation) ንደማይሰጣቸውና ሁኔ ው ለችግር ንደሚዳርጋቸው ከየሐኪሞቹ ጋር ከተደረገ ውይይት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

118. የሥልጠና አለመኖርን አስመልክቶ የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል አምስተኛ አመ ዊ ጉባኤ /ነሐሴ 2001/ ላይ ንደተገለፀው የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ከአርሶ አደሩ ጋር ቀርቦ ተነጋግሮና ተወያይቶ

ለመሥራት የኮሙዩኒኬሽን ዕውቀት ጥረት ያለባቸው በመሆኑ ና ሥልጠና መስጠት ንዳለበት፤ አስተሳሰባቸውንና አመለካከ ቸውን መለወጥና ተነሳሽነ ቸውን ማጐልበት የሚያስችል ሥራም መሰራት ንደሚኖርበት ተገልጿል፡፡ ይሁንና ይህ የኦዲት ሥራ በመከናወን ላይ በነበረበት 2002 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ተፈፃሚ አለመሆኑን ነው፡፡

119. የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴርም ሆነ የክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮዎች ካለባቸው የሥራ ላፊነት አንዱ የ ንስሳት አርቢውን ህብረተሰብ ና በዘርፉ የተሰማሩትን ሞያተኞች ግንዛቤ የማስጨበጥና በሥራ ላይ ንዲውሉ የሞያ ድጋፍ የማድረግ ተግባራት ሆኖ ሳለ በተገቢው መንገድ ተፈፃሚ አለመደረጉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

120. የ ንስሳት ሀብት ልማቱን ውጤ ማ ለማድረግ የአርብቶ አደሩና አርሶአደሩ ንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ የልማት ሠራተኞችና ሞያተኞች ግንዛቤ መዳበርና በ ውቀት መጐልበት ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑ ሊ መንበት ይገባል፡፡

## II. <u>በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስላለው ቅንጅ ዊ አሰራርና የመረጃ አያያዝ በተመለከተ፡-</u>

### <u>በ ንስሳት ሐብት ልማት ዙሪያ ብሔራዊ የጋራ ጉባኤ ስለመኖሩ</u>

121. የአገሪቷን የ ንስሳት ሐብት ልማት ለማፋጠንና ከ ንስሳት ዘርፉ የሚጠበቀውን አስተዋፅኦ ውን ለማድረግ ንዲያስችል የፌዴራል ና የክልል መ/ቤቶችን በመደበኛነት የሚያገናኝ የጋራ ጉባኤ /የምክክር መድረክ/ ሊኖር ይገባል፡፡

122. ይሁን ንጂ በኦዲቱ ወቅት ንደተረዳነው፤ በ ንስሳት ሐብት ልማት ዙሪያ ብቻ ላፊነት ያላቸው የፌዴራል ና የክልል መ/ቤቶችን በመደበኛነት የሚያገናኝ የጋራ ጉባኤ/የምክክር መድረክ/ አለመመሥረቱን ነው፡፡ ይኸውም በፌዴራል ደረጃ የግብርና ሚኒስቴር፤ በ ያንዳንዱ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥ ት፤ ንዲሁም በአዲስ አበባ ና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮች በሚገኙ የግብርናና ገጠር ልማት መ/ቤቶች አማካኝነት የ ንስሳት ሐብት ልማት ሥራው የተከናወነ የሚገኝ ሲሆን በ ንስሳት ሐብት ልማቱ ላይ ብቻ በማተኮር የጋራ ጉዳዮች ላይ ለመመካከርና ውሣኔ ለማስተላለፍ የሚያስችል የጋራ ጉባኤ ያልመሠረተ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. ነገር ግን በበጐ መልኩ ሊጠቀስ የሚችለው በ 1998 ዓ.ም የተቋቋመው “የፌዴራል ግብርናና ገጠር ልማት አካላት ግንኙነት ካውንስል” ሲሆን ተሰብሳቢዎቹም የፌዴራልና የክልል ግብርና ምርምር ተቋማት፤ የክልል ግብርናና ገጠር ልማት ካውንስል ሰብሳቢዎች፤ ቡና አምራች ማህበር፤ ምርጥ ዘር ድርጅት፤

ዩኒቨርሲቲዎች፤ አለም አቀፍ የ ንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት፤ መንግሥ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የዘር አምራች ማህበር የመሳሰሉት በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ አካላት የሚሳተፉበት ካውንስል ነው:: ካውንስሉ በግብርና ሚኒስቴር የበላይ ላፊዎች የሚመራ ሲሆን፤ በአጠቃላይ የግብርና ዘርፍ ላይ በመወያየት ውሳኔዎችን ያሳልፋል::

124. ካውንስሉ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚያደርግ መሆኑ ከቃለ ጉባኤ መረዳት የተቻለ ሲሆን የአንድ ወይም የሁለት ቀናት ውይይት ያደርጋል:: ለምሳሌ ከሚያዝያ 1-2 /2001 ዓ.ም፣ ነሐሴ 29/2001፣ ሚያዝያ 14-15/2002 ይጠቀሳሉ:: በነኚህ የውይይት ስብሰባዎች ግብርናን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ ማለትም የማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭትን፣ የቴክኖሎጂ ማስፋፋት፣ የአፈር ልማት፣ የሰብል አሰባሰብ፤ የምርጥ ዘር አቅርቦትና ሥርጭት፣ የመስኖ ልማት፣ የ ንስሳት ዝርያ አቅርቦት፣ የመኖ ና የ ንስሳት ተዋፅኦ ግብይት፣ የቡና ልማት፣ የመጤ አረሞች፣ የ ንሰት ተክል በሽ ፣ የግብርና መረጃ አሰባሰብ፣ የ ንሰሳት ጤና ወዘተ በ ያንዳንዱ ስብሰባ ወቅት የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው:: በነኚሁ ስብሰባዎችም ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮችም፤ ሰፊውን የውይይት ጊዜ ንዲያገኙ ይደረጋል:: ለምሣሌ በ2000 ዓ.ም በዓለም ላይ ስለደረሰው የምግብ ዋጋ መናርና በአገር ላይ ስለሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ የበልግ ዝናብ ጥረት ላይ ያተኮረ ሲሆን በ2001/2002 ደግሞ ትኩረት ለ ንስሳትና ንስሳት ተዋፅኦ የሚል ነበር::

125. ከዚህ የካውንስሉ ግንኙነት መገንዘብ ንደተቻለው የግብርና ዘርፍ በሙሉ የሚዳስስ መሆኑን ነው:: ግብርና ከንብ ርባ ፣ የዶሮ ልማት፣ አሣ፣ በግና ፍየል፤ አዝ ርትና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ የ ንስሳት ሀብት ልማት ላይ ብቻ ጊዜ ወስዶ በጥልቀት ለመወያየት፣ ችግሮችን ለመለየት፣ የመፍትሄ ርምጃ ለመውሰድና የ ቅድ ክንውን የጋራ ግምገማ፣ የመሥክ ሥራ ማከናወንና የዘርፉን አስተዋፅኦ ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችል የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ለማከናወን በቂ ሆኖ አልተገኘም:: በአመ ዊ ጉባኤው ላይ የሚገኙት ተሣ ፊዎችም ቢሆኑ ከተለያዩ የግብርና ዘርፍ በመሆኑ የ ንስሳት ሐብት ዘርፉ በቂና ተዛማጅ ሞያተኞች ላይወከሉለት የሚችልበት አጋጣሚም ከፍተኛ ሆኖ አግኝተነዋል:: የ ንስሳት ዘርፉ በራሱ ሰፊ ና ውስብስብነት ያለው በመሆኑ ራሱን የቻለ እና በእንስሳት ሀብት ልማቱ ላይ ብቻ የሚመክር የጋራ ጉባኤ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝተነዋል::

126. ጉዳዩን አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ያቀረብንላቸው የሥራ ላፊዎች ማለትም በግብርና ሚኒስቴር የ ንስሳት ሐብት ከፍተኛ ሞያተኛ፣ የኦሮሚያ የ ንስሳት ጤናና ገበያ ኤጀንሲ ተወካይ፣ የአማራ ክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የግብርና

ቴክኖሎጂ ብዜትና የግል ባለሀብት ድጋፍ ዘርፍ ላፊ በሰጡት መልስ በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመወያየትና ውሳኔ ለማስተላለፍ የሚያስችል የጋራ ምክክር መድረክ አለመኖሩን ነው፡፡ ነገር ግን ለምን ንዳልተመሰረተ በምክንያትነት ያቀረቡት መልስ የለም፡፡

127. የጋራ ጉባኤ በመመሥረት የምክክር መድረክ ንዲኖር ማድረግ በ ንስሳት ሐብት ልማት ዘርፍ ላለው ሁለንተናዊ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ገዛ ያለው ስለመሆኑ በርካ ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በ ንስሳት ሐብት ልማቱ ላይ ያሉ ችግሮችን የመለየት፣ ለአተገባበር በሚያመቹ መልኩ በቅደም ተከተል (Priority) የመለየትና የመፍትሄ አማራጮችን የመንደፍ፣ በ ቅዶች ላይ /በረጅም ጊዜ ና አመ ዊ/ የመምከርና የጋራ መገምገሚያ ስልት የማዘጋጀት፣ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶችን የመንደፍና የመተግበር፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሥርጭት ጉዳይን የመለየትና የመወሰን፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን የማሰባሰብና የመለዋወጥ ንዲሁም የሥራ ድግግሞሽን የማስቀረት... ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

128. የሥራ የምክክር መድረክ አለመኖር ቢያንስ ከላይ በጥቂቱ የተጠቀሱትን የልማት ሥራዎች አስተዋፅኦ ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት በየትኛው አካባቢ የትኛው ምርጥ የ ንስሳት ዝርያ መባዛት ንዳለበት ባለመወሰኑ ለአርቢው ሕብረተሰብም ሆነ ለኢንቨስትመንት የምክር አገልግሎት ለመሥጠት አስቸጋሪ ሆኖ ለመገኘቱ፣ በ ንስሳት ጤናና ልማቱ ዙሪያ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለማለዋወጥና ግንዛቤ ለማግኘት አለማስቻሉ፣ አጣዳፊነት ያላቸውን የክትባት ሥራዎች፣ ተጐራባች አካባቢዎች በመተባበር ርምጃ ለመውሰድ አለመቻላቸው፣ በግጦሽ መሬት ላይ አገራዊ የሆነ አዋጅም ሆነ ደንብና መመሪያ አለመኖር፣ በበረት አሰራር፣ መኖ አያያዝና የመጠጥ ውሃ ለመሳሰሉት ጉዳዮች ደረጃ(Standard) አለመዘጋጀቱና የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ የመኖ ባንክ አለመኖር፣ ለሥራ የሚያገለግሉ መመሪያዎች አለመዳረስ /ለምሳሌ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ ዞን የመኖ ተክሎች አይነትና አመራረት መመሪያ ያለ ሲሆን በኦሮሚያ ቦረና ና ሰሜን ሸዋ ዞኖችና ወረዳዎች አለመኖር፣ በአማራ ክልል ደግሞ ጭራሹንም አለመኖር ሊጠቀሱ የሚችሉ ንደሆኑ ይገመ ል፡፡



ፎቶ 20፡ ሙከጡሪ አካባቢ የሰላሌ ወተት ልማት ድርጅት ንብረት የሆነ በሰዎች መተላለፊያ ቦ የተቀመጠና መጠለያ ያልተዘጋጀለት አግባብነት የሌለው የመኖ አያያዝ ሁኔ ን የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 21፡ በኦሮሚያ ሰሜን ሸዋ ዞን ሙከጡሪ አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎች ንብረት የሆነ ደረጃውን ያልጠበቀ የበረት አሰራር የሚያሳይ ፎቶ፡፡

**129. የ ንስሳት ሀብት የጋራ ጉባኤና የምክክር መድረክ መመሥረት የ ንስሳት ሐብት ልማትን ለማፋጠን፣ በአየር ንብረት ለውጥና በሌሎች ምክንያቶች ሊከሰት**

የሚችለውን ችግር ለመከላከል የጋራ ሐይል የሚፈጥር በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: የ ንስሳት ብዛቱ አገሪቷ በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃ የምት ወቅበትና ለአገር ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚችል ዘርፍ በመሆኑ ትኩረቱም አሁን ካለበት ከፍ ሊል ይገባል::

<u>በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ የመረጃ ሥርዓት ስለመኖሩ</u>

130. ለ ንስሳት ሀብት ልማቱ ውጤ ማነትና ዘላቂነት መረጃ የሚጠናቀርበትና የሚሰራጭበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል:: የመረጃ ሥርዓቱም ከወረዳ ጽ/ቤቶች ጀምሮ በተዋረድ የክልል ቢሮዎች ና የግብርና ሚኒስቴርን ሊያካትት ይገባል:: የሚጠናቀረው መረጃም ወቅ ዊ ሁኔ ዎችን የሚያሣይ መሆን ይኖርበ ል::

131. ይሁን ንጂ በወረዳ ደረጃም ይሁን በክልል ቢሮዎችና በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከ ንስሳት ሀብት ልማት ጋር በተያያዘ መረጃ የሚጠናቀርበት፤ ልውውጥ የሚደረግበትና ለተጠቃሚዎችም ዝግጁ የሚሆንበት ሥርዓት ያልተዘረጋ ሆኖ ተገኝቷል:: በዚህም ምክንያት የዳልጋ ከብቶች ብዛት፣ ዝርያ ና ሥርጭትን፣ የ ንስሳት ሞያተኞች ብዛት፣ የሞያ አይነትና ሥርጭት፣ የክሊኒኮች ብዛት፣ አይነትና ሥርጭት፣ የመኖ አቅርቦት መጠን፣ አይነትና ሥርጭት፣ የግጦሽ መሬቶች ብዛትና ሥርጭት፣ የመኖ ማቀነባበሪያዎች ብዛት፣ አቅምና ሥርጭት፣ በየጊዜው የተሰጡ ሥልጠናዎች፣ የ ንስሳት በሽ አይነት፣ ሥርጭትና የሞት መጠን፣ ለ ንስሳት የተሰሩ የውሃ ገንዳዎች ብዛትና ሥርጭት ወዘተ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም::

132. የመረጃ መኖር ለውሣኔ አሰጣጥም ሆነ ሐብትን ለማስተዳደርና የትኩረት አቅጣጫን ለመወሰን ንዲሁም የሥራ ቅድን ተፈፃሚ ለማድረግ አይነተኛ መሣሪያ መሆኑ ትኩረት ያልተሰጠው ሆኖ ተገኝቷል:: በመሆኑም ለኦዲቱ ሥራ ዓመ ዊ አማካኝ የ ንስሳት ሞት መጠን በመቶኛ(mortality rate)፣ በወረዳ ክልልና አገር ደረጃ ለማወቅ፤ የመኖ ፍላጐትና አቅርቦት መጠንን ለመለየት፤ ምርጥ ተሞክሮዎችንና የሀብት ሥርጭትን ለመገንዘብ፤ ወዘተ አላስቻለም:: በዚህም ምክንያት በሀብት አጠቃቀም ላይ ያለውን የሥራ አፈፃፀም ደረጃ ለመገምገም፤ በየዓመቱ ያለውን አካሄድ(trend) ለማወቅ፤ ክፍተቶችን(gaps) ለመለየት፤ የጥሩም ሆነ ደካማ ምክንያቶችን ለማወቅ የሚያስችል አሠራር ሆኖ አልተገኘም::

133. ስለሁኔ ው ለግብርና ሚኒስቴር የድንበር ዘለል በሽ ዎች ቁጥጥር ከፍተኛ ባለሙያ ጋር በተደረገ ቃለምልልስ፣ አመ ዊና ሀገራዊ የዳልጋ ከብቶች ሞት መጠንን የሚያሣይ መረጃ የማይጠናቀር መሆኑን ሲገልፁ፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የ ንስሳት ሀብት ባለሞያ በሰጡትም መልስ ደግሞ ስለ ዳልጋ ከብቶች ብዛት፤ የመኖ ጉዳዮችና ሌሎች የ ንስሳት ሀብትን በተመለከተ

መረጃ ንደሌለ፤ ለዚህም ምክንያቱ ወጥ የሆነ የመረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፤ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ በአለም የምግብና ርሻ ድርጅት/FAO/ ድጋፍ ሰጪነት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱና በማዕከላዊ ስ ትስቲክስ ኤጀንሲ አማካኝነት ጅምር ሥራዎች የተከናወኑ መሆኑን አብራርተዋል። በየወረዳው ጽህፈት ቤቶች በመሥክ ሥራው ወቅት በተደረገ ቃለምልልስም መረጃ የሚጠናቀርበት ሥርዓት አለመኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል። ከየክልል ቢሮዎች ጋር በደብዳቤ በተደረገ ግንኙነት ከትግራይ ክልል በስተቀር የዳልጋ ከብቶችን ብዛት ለመከ ተል የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱን ገልፀዋል።

134. ከዚህም በተጨማሪም የድንበር ዘለል በሽ ዎች የፍንዳ ክስተትን ለመከ ተል ንዲያስችል የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር በመላው አገሪቱ ከሚገኙ የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች በየወሩ የተሞላ የሚላክለት ቅጽ አዘጋጅቶ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት /ከድንበር ዘለል በሽ ዎች ጋር ብቻ በተያያዘ/ የዘረጋ ቢሆንም፣ መረጃውን መላክ ከሚገባቸው ከ60 በመቶ በላይ መረጃ የማይልኩ መሆኑን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተገልጿል።

135. ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ካለው የአሰራር ሥርዓት ለመገንዘብ የተቻለው፤ ለመረጃ መላክ፣ አሰባሰብ፣ ክትትል፣ ማጠናቀርና ለሥራ ዝግጁ የማድረግ ጉዳይ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ነው። ምክንያቱም በ ያንዳንዱ ቀበሌ ደረጃ በየዘርፉ የተለያዩ የልማት ሠራተኞች የሚገኙ ሆኖ ሳለ መረጃን ከምንጩ ጀምሮ በቀላሉ ለማሰባሰብ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ ነው። በተጨማሪም ያለንበት የኢንፎርሜሽን ዘመን መሆኑና መረጃ ዋጋ ያለው፤ ለአገር ልማት አገልግሎት ላይ ሲውል ምርት ሊያስገኝ የሚችል ቢሆንም ትኩረት አለመሰጠቱ አግባብ ሆኖ አልተገኘም።

136. የተጠናቀረ፤ ወቅ ዊ ሁኔ ዎችን የሚያመላክት፤ ትክክለኛና ለሥራ ዝግጁ የሆነ መረጃ ስከሌለ፤ የሀብት ብክነትንና የሥራ መደራረብን/over lap/ የሚያስከትል፤ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያዳግት፤ ሥራን በብቃት ለማከናወንና ሥኬ ማ ለመሆንም አዳጋች መሆኑ መ ወቅ አለበት። በተጨማሪም የመረጃ አለመኖር በ ንስሳት ሀብት ልማቱም ሆነ በሌሎች ዘርፎች የሚደረገውን የምርምር ሥራ የሚያደናቅፍ፤ በልማቱም ለመሰማራት የሚፈልጉ ኢንቨስተሮችን ተነሳሽነት የሚጐዳ፤ የተጠያቂነት መርህንም የሚቃረን በመሆኑ አስቸኳይ የመፍትሄ ርምጃ ሊወሰድለት ይገባል።

# ክፍል ሶስት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

## I. ለዳልጋ ከብት ሀብት ልማት የሚከናወነው የመኖ፣ ውሃ ና ግጦሽ መሬት አቅርቦት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የግንዛቤ መዳበርና ሥልጠናን በተመለከተ፡-

### ከፍላጐት ጋር የተመጣጠነ የዳልጋ ከብት መኖ አቅርቦትን በተመለከተ

137. የመኖ አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ና የክልል ቢሮዎች ንዲሁም የመኖ ልማት ማህበር በጋራ ና በተናጠል ስልት በመንደፍ አፋጣኝ ርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ርምጃውም የመኖ ዘር ማሰራጫ ጣቢያ ማቋቋም፤ የመኖ አምራች ማህበራትን ማደራጀትና ድጋፍ መስጠት፤ የተፈጥሮ ግጦሽን መንከባከብና ማልማት፣ የተሻሻሉ መኖዎችን በስፋት ማምረት ና የመኖ ዘር ማባዛትና ማሰራጨት ተግባራት የሚያካትት ና በ ቅድ በመመሥረት ተፈፃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡

### ለአደጋ ጊዜ የሚሆኑ የመኖ ባንኮች ስለመኖራቸው

138. በአደጋ ምክንያትና በወቅቶች መፈራረቅ በተለይ በበጋ ወቅት የሚከሰተውን የመኖ ጥረት ለመከላከል ቅድመ አደጋ መከላከል ስትራቴጂን ለመከተል ይረዳ ዘንድ የተወሰኑ መሬቶችን በመኖ ንዲለሙ ለማድረግ፤ በዕቅድ የተያዘውም ሆነ ሌሎች የመኖ ባንኮች በአስቸኳይ የሚቋቋሙበት ሁኔ ሊመቻች ይገባል፡፡

### ልቅ ግጦሽን የመቆጣጠርና በዘመናዊነት የመተካት ሥርዓትን በተመለከተ

139. የግብርና ሚኒስቴር ንዲሁም የክልል ቢሮዎች በጋራ ና በተናጠል የግጦሽ መሬት ማልማትና የአጠቃቀም ስልት ና መመሪያ በማውጣት ዘመናዊ የግጦሽ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህንንም ውን ለማድረግ የግጦሽ መሬት አስተዳደር መመሪያ በአስቸኳይ ተዘጋጅቶ ለ ያንዳንዱ ጉዳዩ ለሚመለከተው አስፈፃሚ አካል ና አጋር ድርጅቶች ንዲደርስ በማድረግ አርብቶአደሩ፣ ከፊል አርብቶአደሩ ና አርሶ አደሩ በሙሉ ንዲገነዘበውና ተፈፃሚ ንዲያደርግ መደረግ አለበት፡፡ ለአፈፃፀሙም የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡

## ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረም የማስወገድ ና የማልማት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ

140. የ ንስሳት መኖ ጥረትን ለመቅረፍ ከሚያስችሉ መንገዶች አንዱ አላስፈላጊ አረሞችን ከግጦሽ መሬት ላይ ማስወገድ በመሆኑ፤ ከግጦሽ መሬት ላይ አላስፈላጊ አረም የሚወገድበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ አላስፈላጊ አረሞችን ለማስወገድ ወጥነት ባለው መንገድ ሀገራዊ ንቅናቄ በመፍጠር (አርብቶአደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተሳ ፊ የሚሆኑበት) ዘላቂነት ባለውና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሠራር አላስፈላጊ አረሞች ከግጦሽ መሬት ላይ ተወግደው ለተፈለገው አገልግሎት የሚውሉበት ሁኔ በአስቸኳይ መመቻቸት አለበት፡፡

## በግጦሽ ሥፍራዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚሆን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተመለከተ

141. በአርብቶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ዘንድ በሚገኙ የግጦሽ መሬት አካባቢዎች ለዳልጋ ከብቶች የሚውል ንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት መኖር አለበት፡፡ በውሃው ላይ የናሙና ምርመራ የሚደረግበትና ንፅሕናውም የሚረጋገጥበት የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ አርብቶአደሩ፣ ከፊል አርብቶአደሩና አርሶ አደሩ በንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የንፅሕና ክትትልና ቁጥጥር ላይ ተሣ ፊ ና ተጠያቂም የሚሆንበት አሠራር ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በሌለበት አካባቢ የወንዝ ውሃን የሚጠጡ ንስሳትን ከአደጋ ለመጠበቅ ንዲያስችል የተፋሰስና የወንዝ ዳርቻ ሥፍራዎች በ ፅዋት ንዲሸፈኑና ደህንነ ቸው ንዲጠበቅ መደረግ አለበት፡፡ በወንዞች ውስጥ የልብስ፣ ገላ ና መኪና ጥበት በማናቸውም አይነት ምክንያት መከናወን የለበትም፡፡ የተዘጋጁ የመጠጥ ውሃ ማከማቻ ኩሬዎች ውስጥ ከብቶች በቀጥ ገብተው መጠጣት አይኖርባቸውም፡፡ ይህንን ተግባር ውን ለማድረግ የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር፣ የክልል ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን መመሪያ በማዘጋጀትና በማሰራጨት በአስቸኳይ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

## የዳልጋ ከብቶች ጤና አገልግሎት ስለመዳረሱ ና አጥጋቢ ስለመሆኑ

142. የ ንስሳት ጤና ተቋማት በሙሉ አቅማቸው መስራት ንዲችሉ በሰው ይል፣ በህክምና መገልገያ መሣሪያ፣ በቁሳቁስ ና መድሀኒት አቅርቦት ንዲሟላ መደረግ አለበት:: የአካባቢውን የ ንስሳት ስርጭት መሠረት ያደረገ ና በጥናት ላይ የተመረኮዘ የ ንስሳት የጤና ተቋማት ንዲገነቡ መደረግ ይኖርበ ል:: ይህን ተግባራዊ ለማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሉት የግብርና የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬትና የ ንስሳትና ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ከሌሎች የሚመለከ ቸው የክልል ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የግንኙነት ሥርዓት በመዘርጋት ተፈፃሚ ሊደረግ፣ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችም የሚከናወኑበት አሠራር ተግባራዊ ሊሆን ይገባል:: በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ በሽ ዎችን የመለየት፣ የተቀናጀ የበሽ ዎች መከላከልና መቆጣጠር ሥራ በመደበኛነት የሚከናወንበት፤ የተጠያቂነት ሥርዓትም የሰፈነበት አሠራር በአስቸኳይ ተግባራዊ መሆን አለበት::

## የአገር ውስጥ የዳልጋ ከብት ዝርያ የማሻሻያ ተግባርን በተመለከተ

143. የተሻለ የሥጋና የወተት ምርት ያላቸውን ሀገር በቀል የዳልጋ ከብቶች የዝርያ መለየት ጥናትን ከማከናወን ጀምሮ በጥናቱ መሠረት የአካባቢ ምርጥ ዝርያዎች በመለየት ማባዛት፤ የተሻለ ምር ማ የሆኑ የሀገር ውስጥና ውጭ አገር ዝርያዎችን ከአካባቢው ዝርያዎች በማዳቀል ለአምራቹ ማሰራጨት፤ ለገበያ ተፈላጊ የሆኑ የዳልጋ ከብት ዝርያዎችን በጥራትና በብዛት ማምረት ንዲቻል በምርምር የተደገፉ ሥራዎች መከናወን ይኖርባቸዋል::

## ለሞያተኞችና ለአርብቶ አደሮች የሚሰጥ የግንዛቤ ማዳበሪያና ስልጠናን በተመለከተ

144. በ ንስሳት ሀብት ልማት ላይ የተሰማሩ ሞያተኞች ለስራቸው ገዛ የሚያደርግ የ ውቀትና ክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና የሚያገኙበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል:: በከብት ርባ ላይ የተሰማራው የህብረተሰብ ክፍል ዘመናዊ የከብት ርባ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለው የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥልጠና የሚያገኝበት ሥርዓት ሊዘረጋና በአስቸኳይ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባል:: ለሞያተኞች፣ ለአርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮችና አርሶ አደሮች የሚሰጠው ስልጠናም ወጥነት፣ ዘላቂነት ንዲኖረው፣ ብቃትና ሥኬ ማነቱንም ለማረጋገጥ ንዲያስችል በቅድመ ጥናት ላይ የተመረኮዘ፣ ያመጣውን ውጤትም ለመከ ተል የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋለት ይገባል::

## II. በዳልጋ ከብት ሀብት ልማት ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስላለው ቅንጅ ዊ አሰራርና የመረጃ አያያዝ በተመለከተ:-

### በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ብሔራዊ የጋራ ጉባኤ ስለመኖሩ

145. በአጠቃላይ በ ንስሳት ሀብት ልማቱ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ንዲያስችል በ ንስሳት ሀብት ልማቱ ላይ የሚመክር ብሔራዊ የጋራ የምክክር መድረክ ቢቋቋም በዘርፉ ላይ ያሉ መሠረ ዊ ችግሮች ና አንገብጋቢ ጉዳዮችን በቅደም ተከተሉ የሚለይበት፣ የመፍትሔ ርምጃ በጋራ ና በተናጠል የሚወሰድበት ሥልት የመንደፍና ተፈፃሚ የማድረግ አቅምን ለመፍጠር ከማስቻሉም በላይ የሥራ ድግግሞሽንና የሀብት መባከንን ሊያስቀር ይችላል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ የሚመለከ ቸው የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ና የክልል ግብርና ቢሮዎች ላፊዎች ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ሊወያዩበትና ውሣኔ ላይ ሊደርሱበት ይገባል፡፡

### በ ንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ የመረጃ ስርዓት ስለመኖሩ

146. ከ ንስሳት ሀብት ልማት ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆነ፣ ወቅ ዊና አስተማማኝ መረጃን በተፈለገው አይነት፣ ጊዜና በ ማግኘት የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ የመረጃ ሥርዓቱም በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር፣ በክልልና በወረዳ ግብርና ቢሮዎች፣ ንዲሁም አጋር ድርጅቶችን የሚያስተሳስርና ወጥነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡ ሥርዓቱን የመዘርጋት ተግባርም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአስቸኳይ ሊደራጅና ለአገልግሎት ሊውል ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለስራችን መቃናት ትብብር ላደረጉልን በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር የግብርና የኤክስቴንሽን ዳይሬክቶሬት፣ የ ንስሳትና ዕፅዋት ጤና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፣ የግብርና ምርምር ተቋም ባለሙያዎች፣ የኢትዮጵያ ንስሳት መኖ ኢንዱስትሪ ማህበር ና የክልል ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮዎች ባለሙያዎችና ንዲሁም የዞንና የወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ላፊዎች ምስጋና አናቀርባለን፡፡